ምዕራፍ 2

የወንጌል ስርጭት መመሪያዎች

ፍራንና እኔ ከመጋባታችን ስድስት ወራት በፊት፥ የፍራን አባት ቤት ሊሠሩልን ማቀዳቸውን ገለጹልን። ለቤቱ ግንባታ የታቀደው መሬት ብዙ ዝግጅት የሚያስፈልገው ነበር። እኔና የፍራን አባት በመሬቱ ላይ የነበሩትን ትላልቅ የባሕር ዛፎች ለማስወገድ ተግተን መሥራት ነበረብን። ከዚያ በኋላ ደግሞ መሬቱን ለመሠረት ሥራ ማዘጋጀት ይቻል ዘንድ መሬቱን የሚቆፍር ቡልዶዘር መጣ። በመጨረሻ የቁፋሮ ሥራ ተካሄዶ መሠረቱን የሚደግፉ ብረቶችን የማሰር ሥራ ተጠናቀቀ። ጉድጓዶቹ በምን ያህል ጥልቀትና ስፋት መቆፈር እንዳለባቸው ስለማላውቅ፥ እየተቃረበ ላለው ጋብቻችን ስለቸኮልሁና ስለጓጓሁ፥ የመሠረት ሥራው በፍጹም የማይገፋ ሆነብኝ። የግንባታው ሥራ እስኪጀመር ቸኮልሁ። ቤቱ እስኪያልቅ ድረስ መጠበቅ አቃተኝ። ለግንባታው ሥራ የሚያስፈልጉ ጥብቅ ቅድመ ሁኔታዎችና ይህን የሚያረጋግጡ የከተማው ሕንጻ ግንባታ ተቆጣጣሪዎች ባይኖሩ ኖሮ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ነገሮች በሚገባ ሳይዘጋጁ እጀምር ነበር።

ከፍል አንድን ማለትም ከዘፍጥረት እስከ ዕርገት የሚገኙትን ታሪኮች ለማያምኑ ሰዎች በማስተማር የወንጌል ስርጭት ወደምትጀምርበት ጊዜ ስትቃረብ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማስተማር የሚያስፈልገውን ዝግጅት ሁሉ ለማጠናቀቅህ ራስህን ጠይቅ። አንተም ሆንህ ሕዝቡ በበቂ ሁኔታ ከመዘጋጀታችሁ በፊት ማስተማር ለመጀመር ልትገፋፋ ትችላለህ። ለመሆኑ የወንጌል ስርጭት ለመጀመር ጊዜ መድረሱን የሚጠቁሙ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ቋንቋ

የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ጊዜ ለመድረሱ ከሁሉ የላቀ ማረጋገጫ፥ የአካባቢውን ሕዝብ ቋንቋ ለመረዳት፥ በጥሩ ሁኔታ ለመግባባትና በግልጽ አሳባችንን ለመግለጽ መቻላችን ነው። በዚህ ተከታታይ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል በአድማጮቻችን አእምሮ ውስጥ እምነትንና ሥራን በተመለከተ ሊፈጠር የሚችለውን ግራ መጋባት ለመቋቋም ንጹሕ ወንጌል መስበክ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተመልክተናል። ወንጌልን የተረዳንበትና የምናቀርብበት መንገድ ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን፥ ቋንቋቸውን በሚገባ ከማወቃችን በፊት ማስተማር ብንጀምር አድማጮቻችን የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በተዛባ መንገድ መረዳታቸው አይቀርም። ብዙ የገጠር ሰዎች የክርስትናን ደኅንነት መልእክት በተመለከተ ግራ የተጋባ አሳብ እንዲኖራቸው ምክንያት የሚሆኑ ሁለት ዐበይት ምክንያቶች

የአካባቢውን ሕዝብ ቋንቋ በሚገባ ያለማወቅና ወንጌልን ከተጻፈበት በተለየ አቀራረብ ማስተማር ናቸው።

ቋንቋውን በሚገባ ከማወቅህ በፊት እንድታስተምር የሚገፋፉ በርካታ ጫናዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ለማስተማር እጅግ እንድትጣደፍ ሊያደርግህ የሚችል አንዱ ምክንያት ሕዝቡ የደኅንነትን መልእክት እንዲሰሙ ያለው አንገብጋቢነት ነው። በፓላዋን ቋንቋቸውን በማጠናበት ወቅት የነበረኝን ሸክምና ጭንቀት አስታውሳለሁ። አንዳንዴ በእግዚአብሔር ፊት ወድቄ ጌታ እውነትን መማር ለሚያስፈልጋቸው ለእነዚህ ሰዎች ቃሉን የማስተምርበትን ዕለት እንዲያፋጥን በእንባ ዘለላዎች ታጅቤ እጸልያለሁ።

ሌላው ምክንያት የአካባቢው ሰዎች ከመጣንበት ምድር ጨርሶ የተለየ እጅግ ከባድ ሊባል በሚችል አካባቢ ከእነርሱ ጋር ለመኖር የመጣንበትን ትክክለኛ ዓላማ እንድንነግራቸው አጥብቀው የመጠየቃቸው ጉዳይ ነው። ሌላው ግፊት ደግሞ የተላከንበትን የወንጌል ሥራ በገንዘብ የሚደግፉ ክርስቲያኖች የወንጌል ስብከትን ሥራ ገና እንዳልጀመርን ቢረዱ ምን ይሰማቸው ይሆን? የሚለው ጭንቀት ነው። ከእነዚህ ሁሉ ግፊቶች ባሻገር የቅዱሳት መጻሕፍትን መልእክት በሚገባ በቋንቋቸው ለማስተላለፍ በማትችልበት ደረጃ ወደ ማስተማሩ ፈጥነህ ከመግባት ተጠንቀቅ።

ቀጥለን እርሱ እና አብሮት የሚሠራ አገልጋይ በኤምቤራ ጎሳዎች መካከል የአካባቢውን ቋንቋ በሚገባ ከማወቃቸው በፊት በግፊት ማስተማር በመጀመራቸው ሕዝቡ መልእክታቸውን እንዴት በተዛባ መንገድ እንደተረዳ ዳግ ሹርመርሑርን የተባለ በፓናማ በወንጌል መልእክተኛነት የሚሠራ ሰው ከጻፈው ጽሑፍ በከፊል እናቀርባለን።

«በየካቲት 1982 እኔና ጃሚ እኒማርከ ኑዌቮ ቪጂያ ወደምትባል መንደር ተንቀሳቀስን። በመንደሪቱ መኖር ይቻል እንደሆነ በማለት ወደዚህ የመጣነው ከአንድ ዓመት በፊት ነበር። ጃሚና እኔ ሁለታችንም የመጣነው በጉጉት ነበር። አዲስ የወንጌል መልእክተኞች ስለነበርን በሚቀጥሉት ወራት ምን እንደሚገጥመን አላወቅንም ነበር።

«እኔና ጃሚ እንድናስተምራቸው የሚፈልጉና ክርስቲያኖች ነን የሚሉ አያሌ ሰዎች ነበሩ። ለነገሩ የመጣንበትስ ምክንያት ለዚሁ አልነበር? ሁለታችንም የአካባቢውን የኤምቤራ ቋንቋ አናውቅም ነበር። ስለዚህ በሚገባ እንደማይረዱን ብናውቅም እንኳ በስፓንሽ ቋንቋ ልናስተምራቸው ተገደድን። በሚገባ ልናስረዳቸው ያለመቻላችንን በተረዳን ጊዜ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሆናችንን ተገነዘብን። ይህም ቢሆን እንኳ የጠየቁንን ለማሟላት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ጥረታችንን ቀጠልን።

«ገና ልናስተምርበት በምንችልበት ደረጃ ላይ ባንሆንም የኤምቤራን ቋንቋ እየተረዳን መምጣት ስንጀምር፥ ክትምህርታችን ምን ተረድተው እንደነበር መጠየቅ ጀመርን።» በመጋቢት 1983 በእኔና ሲዛር ኮንትሬራ በሚባል ሰው መካከል የተደረገው የአሳብ ልውውጥ የሚከተለው ነው፦

«እግዚአብሔር አባት አለውን?» በማለት ጠየቅሁት።

«እኔ አላውቅም፤ ነገር ግን ማርያም እናቱ እስከ ሆነች ድረስ አባት ሳይኖረው አይቀርም» በማለት መለሰልኝ።

ቀጥሎ ስለ ዓለም አፈጣጠር ጠየቅሁት።

«እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ» በማለት ጀመረ። «ደግሞም በውስጧ ያሉትን ሁሉ ፈጠረ። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፥ በመጀመሪያ ሁሉም ጨለማና ውቅያኖስ ነበር። ቀጥሎም ውኃዎቹን በመለየት ምድረን ፈጠረ።›

«ብርሃንስ እንዴት ተፈጠረ?» በማለት ጠየቅሁት።

«ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ ጨለማ ነበር። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነው ይላል» በማለት መለሰልኝ።

«ከኢየሱስ በፊት ግንም ሰው አልነበረምን?› በማለት ጠየቅሁት።

«ሰው መኖር አለበት። ነገር ግን የተለዩ ነበሩ። በእርግጥ አላውቅም» በማለት መለሰ።

«የጥፋት ውኃ መቼ ነበር የደረሰው?» በማለት ጠየቅሁት።

«ከኢየሱስ በኋላ እንደነበር እንጂ መቼ እንደነበር አላውቅም» አለ።

ቋንቋቸው የበለጠ እየተረዳን ስንሄድ ምን ያህል ተምታቶባቸው እንደነበር ተገነዘብን። ደኅንነት ማለት ለእነርሱ ኃጢአታቸውን መተውና መልካም ሥራን እየሠሩ ወደ መንፈሳዊ ስብሰባዎች መሄድ ማለት ነው። በኤምቤራ ሕዝብ መካከል ‹አማኝ ነበርሁ› ማለት የተለመደ ነው። አማኝ የሚሆኑበት መሠረታዊ ምክንያት ከጊዜው ችግራቸው ለመላቀቅ ነው። የሚያሳስባቸው በዚህ ሕይወት በሰላም የመኖራቸው ጉዳይ እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት አይደለም።»

እነዚህ ሁለት የወንጌል መልእክተኞች የኤምቤራን ቋንቋ በሚገባ ከተማሩ በኋላ የክፍል 1 ትምህርት ማስተማር ጀመሩ። ውጤቱ ምን ነበር?

ዳግ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፦ «የኤምቤራ ሰዎች ሊያምኑና የቀድሞ ኑሮአቸውን ሊተዉ ከብዱአቸው ነበር። ነገር ግን ክርስቶስን ብቻ ለደኅንነታቸው በማመን ወንዶችና ሴቶች ወደ ጌታ ሲመጡ በማየት ተበረታታን።»

ባህል

የአካባቢውን ባህል የማወቅና በሚገባ የመረዳት ጉዳይ የአካባቢውን ቋንቋ በሚገባ የመረዳትና የመናገር ችሎታን ማጣመር አለበት። በተለይም መሠረታዊ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነታቸውን በሚገባ ለማወቅ ትኩረት መስጠት አለብን። ከምናቀርብላቸው ትምህርት የተነሣ ሊከሰት የሚችለውን አተረጓጐምና የተፃራሪ እምነቶች ደባልነት ቀድመን በማየት አስፈላጊ የማስተካከያ ትምህርት ልንሰጥ የምንችለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው። ባህልን መረዳት አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ ስለ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እምነታቸው ውስብስብ ጉዳዮችንና ትርጉሞቻቸውን ጠንቅቀህ እስከምታውቀው ትምህርቱን ከመስጠት አንዳትታቀብ ተጠንቀቅ። በምታስተምርበት ወቅት ሕዝቡን ያለማቋረጥ ጥያቄ የምትጠይቅና የሚሰጡትንም ምክንያታዊና ግብታዊ ምላሾች በጥንቃቄ የምታደምጥ ከሆነ ስለ ባህላቸው አዳዲስ አውቀቶችን በማግኘት አስተሳሰባቸውን የበለጠ እየተረዳህ ትሄድና መልእክትህን ሊያደበዝዙ የሚችሉትን ማናቸውንም ነገሮች የሚያስተካክሉ ተጨማሪ ትምህርቶችን ለመስጠት ትችላለህ።

ሕዝቡ

በምዕራፍ 1 የተሰጡትን አሳቦች በመከተል ሕዝቡን ለወንጌል ሥራ አዘጋጀተህ እንደሆን ለመወሰን የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ በል፦

- በአጠቃላይ ውይይቶቻቸውና ተግባሮቻቸው እንድትሳተፍ በደስታ ይጋብዙሃል ወይስ ፊት በመንሣት ያገልሉሃል?
- ወደ ቡድናቸው በምትቀርብበት ጊዜ አጠቃላይ ዝምታ ይሰፍናል ወይስ በመልካም ተቀብለውህ የጀመሩትን እንደ ወትሮአቸው ይቀጥላሉ?
- መንፈሳዊ እምነቶቻቸውን ከአንተ ጋር በግልጽነት ለመጫወት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ነፃነት ይሰማቸዋልን?
- በባህላቸውና በሃይማኖታቸው ቀደም ብሎ ያደረባቸው ግምት መሠረቱና ሥልጣኑ ከየት እንደሆነ ለመጠየቅ በየጊዜው የሚያድግ ፈቃደኝነት ይታይባቸዋልን?
- ሕዝቡ መንፈሳዊ ነገሮችን ብዙ አለማወቃቸውን ለመቀበል ያላቸው ግልጽነት እየጨመረ ነውን?

- እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ በየት እንዳለ፥ ምን እንደሚመስልና በቅድመ-ወንጌል ያነሣሃቸውን ሌሎችም ጥያቄዎች መልስ ለማወቅ ያላቸው ፍላጐት እያደገ ነውን?
- የተፈጥሮን አስደናቂነት ለመናገርና አትኩሮትህንም ወደዚያ ለመሳብ የበለጠ ነፃነት እየተሰማቸው ነውን?
- የጠየቅሃቸው መንፈሳዊ ጥያቄዎች በሰው አእምሮ ብርታት ወይም ተፈጥሮን ብቻ በመመልከት በቀላሉ እንደማይመለስና ይልቁንም ይህን ለመመለስ ከሰው የላቀ ከፍተኛና ታላቅ ኃይል እንደሚያስፈልግ ተረድተዋልን?

ምንም እንኳ ለወንጌል ሥራ ሰዎችን ለማዘጋጀት የምትችለውን ሁሉ ማድረግ እንዳለብህና መቀበላቸውን ከሚጠቁሙ ከእነዚህ ግልጽ ምልክቶች አንዳንዶችን እስከምትመለከት የቅድመ-ወንጌል አገልግሎቱን እንዳትጀምር ብገፋፋህም፥ ሰዎችና ባህሎች እንደሚለያዩ መዘንጋት እንደሌለብህ አሳስብሃለሁ። አንዳንዶች ስሜቶቻቸውን ባለመደበቅ በቃል ሲገልጡ ሌሎች ደግሞ በጥንቃቄ ይሰውሩአቸዋል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተዋወቅና ለማስተማር ሕዘቡ እንዲዘጋጁ የተቻለህን ሁሉ አድርገህ የሚሰጡህ ምላሽ ግን እስከዚህም ቢሆን ተስፋ አትቁረጥ፤ ወይም ከውጭ የሚታየውን ነገር አትመልከት። ጌታ ኢየሱስ ሊመጣ ስላለው የእግዚአብሔር መንግሥት፥ «ሴት ወስዳ ሁሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች» (ሉቃስ 13፡21)። ከእግዚአብሔር የሆነ የእውነት መገለጥ ስለማግኘት አስፈላጊነት እንዲያጤኑ ልትቀሰቅሳቸው በሞከርካቸው ሰዎች ሕይወት የሚታየው የእግዚአብሔር ሥራ ይህ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ጥንካሬያቸውን በመስበር የእርሱ እውነት እንደሚያስፈልጋቸው እንዲያዩ ለማድረግ እንደሚችል በእርሱ ታምነህ በወንጌል ሥራ ወደፊት ቀጥል።

በቂ ዝግጅት አላደረግሁም ብሎ መስጋት

መቼ መጀመር አለብን? የሚለውን ጥያቄ ከማለፋችን በፊት ከባድ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለብኝ። አንዳንድ የወንጌል መልእክተኞች ማስተማር ለመጀመር በሁሉም መንገድ ከተዘጋጁ በኋላ እንኳ ሥራውን ለመሥራት አንደሚችሉ አይሰማቸውም። ከፊት ለፊታቸው ላለው ግዙፍ ተግባር ድፍረት ያጣሉ። ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዕርገት ድረስ ያለውን ትምህርት በሌላ ቋንቋ ለማስተማር በፍጹም የማይበቁ ይመስላቸዋል። አንድ ምሳሌ ትዝ ይለኛል። ወንዱንና ሴቷን ልጆቼን መኪና መንዳት በማስተምርበት ጊዜ እጅግ የተጣበበ መስቀለኛ ቦታ ሲደርሱ በራስ አለመተማመን ይሰማቸዋል። እነዚያን የሚያህሉ

መኪናዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች እየተርመሰመሱ መኪናቸውን ለመቆጣጠር የመቻላቸው ሥጋት ያስጨንቃቸዋል። ይህን ለእኔ ሲገልጡልኝ፥ «ከፊት ለፊታችሁ ስላለ ነገር አትጨነቁ። እዚያ ከመድረሳችሁ በፊት በዚያ ላይ አታሽከረክሩም። እዚያ በምትደርሱበት ጊዜ ሁሉም ነገር አሁን ካያችሁት የተለየ ሊሆን ይችላል። ከፊት ለፊታችሁ ያሉት መኪኖችም እየሄዱ ናቸውና አሁን ማድረግ ለሚገባችሁ ነገር ብቻ አስቡ። የወደፊት ውሳኔዎችን ስትደርሱባቸው ታስባላችሁ» እላቸዋለሁ። ሌላው ምሳሌ በራሴ ሕይወት ውስጥ ያለፈ ነው። መኪና መንዳት ለመጀመሪያ ጊዜ በተማርሁበትና ረጅም መንገድ መንዳት ባስፈለገኝ ጊዜ ለመንዳት በጣም የሚያስፈራ ነገር መስሎ ታየኝ። «ይህንን ያህል ርቀት እንዴት ችዬ እነዳለሁ?» ብዬ አሰብሁ። ከዚያ በኋላ ግን፥ ከአንደኛው ኪሎ ሜትር ወደ ሁለተኛው ኪሎ ሜትር እያልሁ ቀስ በቀስ መንዳት እንደምችልና በዚሁ ከቀጠልሁ ደግሞ በመጨረሻ ወዳቀድሁበት ሩቅ ስፍራ መድረስ እንደምችል ተገነዘብሁ። የክፍል አንድን ትምህርት ማስተማር የሚኖርብንም እንዲሁ ነው። ልንመለከታቸው የሚገቡን ጉዳዮች በርካታ መሆናቸውና ወደማጠቃለያው ከመድረሳችን በፊት ብዙ ወራት እንደሚወስድብን የተረጋገጠ ነው። እያንዳንዱ ክፍልና በውስጡ የሚከሰተውን ችግር በጥንቃቄ፥ ትንሽ በትንሽ እያደረግን ሰዎች እስከሚረዱት በግልጽ ማስተማራችንን እያረጋገጥን ከቀጠልን፥ በስኬታማነት እስከመጨረሻው እንዘልቃለን። እንደ ጥንታዊው አባባል «ሳትደርስበት ድልድይህን አትሻገረው።»

እግዚአብሔር በውስጥህ በሚኖረው በመንፈሱ አማካይነት ሙሉ ብቃት እንዳለው በእምነት ከተመለከትህ የአንተ ያለመብቃት ስሜት በአንተ በኩል የሚሠራውን የእግዚአብሔር ቃል ታላቅነትና ኃይል ሊያግድ እንደማይችል አርቀህ አስተውል። «ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳች እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን» (2ኛ ቆሮ. 3፡5-6)። ነገር ግን ይህ በጌታ ላይ ያለን እምነታችን በእኛ በኩል ከኃላፊነት ወደ መዘንጋት ሊመራን አይገባም። ይልቁንም የተመሰከረልን ሠራተኞች እንድንሆን በታማኝነት ልንተጋ ይገባል። «የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ» (2ኛጢሞ. 2፡15)።

የስብሰባ ጊዜ

የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተዋወቅና ከፍል አንድን ለማስተማር ጥያቄዎችን ስትጠይቅ፥ ጠቃሚ ርእሰ-ጉዳዮችን ስታወያይና ከሕዝቡ ጋር መልካም ጎብረት ስታደርግ የነበርህባቸውን ጊዜያት ተጠቀም።

ሰዎች እነርሱን ለመጠየቅ የምታደርገውን ጉብኝት ለውጠህ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጀመርህ እንዳይመስላቸው ይህን ስብሰባ የምትጀምረው በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ደረጃና በወንጌል ስብከት ደረጃ ምንም ዓይነት የጊዜ ክፍተት ሳይኖር ነው።

የስብሰባ ቦታ

የወንጌል ስርጭት በወንጌል መልእክተኛው ቤት ወይም በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ከተጀመረ፥ አንዳንድ የአካባቢው ሰዎች ወደ ወንጌል መልእክተኛው ቤት ወይም ወደ አንድ የተለየ ሕንጻ በመግባታቸው የወንጌል መልእክተኛውን ሃይማኖት እንደተቀበሉና ክርስቲያን እንደሆኑ ሊያስቡ ይችላሉ። ይህ በተለይ እውነት የሚሆነው ከዚህ በፊት እውነተኛ የወንጌል ስርጭት ሳይካሄድ ዳሩ ግን የወንጌል መልእክተኛ ተግባር ተከናውኖ እንደሆነ ነው። ወደ ቤታቸው በመግባት፥ በተቀመጡበት ስፍራ በመቀመጥና ከአካባቢው ባህል ጋር በመግባባት የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በባህላዊ መዋቅራቸው ውስጥ የሚማሩትና የሚለማመዱት እንደሆነ በምሳሌ እናሳያቸዋለን። ሰዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት የምዕራባውያን ሥልጣኔ ተቀጥላና የባህላችን አካል እንደሆነ ወይም ክርስትና በተወሰኑ ቦታዎችና ጊዜያት ብቻ በሳምንት ውስጥ የሚካሄድ ነገር አድርገው የሚያስቡበትን ፍንጭ መጠቆም የለብህም።

ወዳሉበት ስፍራ በመሄዳችን ለወደፊቱ አማኞች ጥሩ ምሳሌን እያሳየናቸው ነው። ወዳልዳኑት ሰዎች ቤተሰብ የወንጌልን መልእክት የማድረስ አስፈላጊነት እናሳያቸዋለን። ሕይወታችንም ሆነ ሥራዎቻችን የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት አገልግሎታችንን የምንሰጠው ሕዝቡ እንደ ባህላቸው በሚሰበሰቡበት ጊዜና ቦታ ሲሆን ነው።

ሰዎች ብዙ ጊዜ በሚሰበሰቡበት ቦታና ወቅት ሄዶ የማገልገሉን አስፈላጊነት ልብ በሚነካ መንገድ ያየሁት በፓፑዋ ኒው ጊኒ ተራራማ ስፍራ የሚገኝ አንድ የወንጌል ጣቢያን በጐበኘሁበት ጊዜ ነበር። የወንጌል መልእክተኞቹ ከቤታቸው በስተጀርባ በምትገኝ አንዲት ትንሽ ክፍል ለረጅም ጊዜያት ሳምንታዊ ሰብሰባዎችን ያካሂዱ ነበር። የአካባቢው ሰዎች ወደዚያ መጥተው ስብሰባ እንዲካፈሉ የሚችሉትን ሁሉ ቢያደርጉም እንኳ የሚካፈሉት ሰዎች ቁጥር ጥቂት ነበር።

ስብሰባ በሚካሄድበት ምሽት የወንጌል መልእክተኞቹ ፋኖስ አብርተው በመሰብሰቢያው ስፍራ አስቀመጡ። ከ 15 ደቂቃ ጥበቃ በኋላ ያላገቡ ወጣት ወንዶች መጡና እየተሽኮረመሙ ወደ ውስጥ ገቡ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥቂት ያላገቡ ወጣት ሴቶች መጡ። ወዲያውኑ ከወንዶች አብዛኛዎቹ ብድግ ብለው በመሮጥ ወጡና ወዲያው ደግሞ ተመለሱ።

በዚህ ጊዜ አብዛኞቹ ሴቶች እያከታተሉ ማቃቸውን ለቀቁ። ከመካከላቸው አንዳንዶቹም ለአፍታ ያህል ወደ ውጭ ወጡ። ቁጭ ብዬ እያየሁ ትምህርቱን መጀመር እንዲቻል በርጋታ ይቀመጡ ይሆንን?! ብዬ ተደነቅሁ።

ሁኔታው ግር ስላለኝና ስላልገባኝ ስለ ስብሰባ ስልታቸው የወንጌል መልእክተኞቹን ጠየቅኋቸው። ወጣቶች እየገቡና እየወጡ ከጥቂት ውይይት በኋላ የወንጌል መልእክተኞቹ ሕዝቡን በሚሰበሰብበት ጊዜና ቦታ ወንጌልን እንደማያስተምሩ ታወቀ። እዚህ አካባቢ በነበረው ሕዝብ ልማድ ወንዶች ብዙ ጊዜ ከሚስቶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በማኅበረሰቡ ቤት እንደሚያድሩ አውቅ ነበር። ስለዚህ ሁለቱን የወንጌል መልእክተኞች ወደ ወንዶች ማኅበር ቤት መሄድ ይችሉ እንደሆነ ጠየቅኋቸው። ይህ እንደሚቻል አረጋገጡልኝ። ስለዚህ እዚህ እነርሱ በሠሩት ቤት ስብሰባ ከማካሄድ በብዙ ቁጥር ወንዶች ተሰብስበው ወዳሉበት የወንዶች ማኅበር ቤት መሄድ እንደሚሻል አሳብ አቀረብሁ። «ሴቶቹን የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እናስተምራቸዋለን?» የሚል ጥያቄ ተነሣ። ሴቶች ወደ ወንዶች ማኅበር እንዲገቡ አይፈቅዱም። ሴቶች ካሉ ደግሞ ወንዶች ወደ ቤት መግባት አይፈቀድላቸውም። ከተጨማሪ ውይይት በኋላ፥ ከሌሎች ወንዶች ጋር በማኅበር ቤት ከመኖር ይልቅ፥ በቤተሰብ ደረጃ ከሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ጋር ለመኖር በወሰኑ አንዳንድ ሰዎች ቤት ልጃገረዶቹ እንዲማሩ ተወሰነ።

እነዚህ ሁለት ወጣት የወንጌል መልእክተኞችን አደፋፍሬ በዚያው ዕለት ይህን መንገድ እንዲሞክሩ አደረግሁ። በዚያ ለነበሩ ልጃገረዶች አዲሱን ቅንጅት በመግለጽ ፋኖሱን ይዘን በሁኔታው እጅግ በተደሰቱት ወጣት ወንዶች እየተመራን ወደ ወንዶቹ ማኅበር ቤት ሄድን። ወንዶቹ ቤት በገባን ጊዜ መቀመጫ ማግኘት አልቻልንም። ወዲያውኑ በአካባቢው ካሉ ቤቶች ሌሎች ወንዶች መጥተው ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ። የተጣበበ ቢሆንም እንኳ ጊዜውና ቦታው ለማስተማር እጅግ ጥሩ ነበር።

ምን ያህል ጊዜ እናስተምር?

ሕዝቡ ለመሰብሰብ ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ በየቀኑም ቢሆን ማስተማርህን ቀጥል። ለሕዝቡ የሚቀርብና ሊማሩት የሚችሉት በርካታ ትምህርት አለ። የበለጠ በተገናኛችሁ ቁጥር ከብሉይም ሆነ ከአዲስ ኪዳን ያቀድኸውን ሁሉ ለማስተማር ዕድል ታገኛለህ።

ለስብሰባ ያለን አመለካከት በሕዝቡ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ስብሰባ ጠርተን በተደጋጋሚ የምንሠርዝ ከሆነ ሰዎችም ይህን ምሳሌያችንን ይከተላሉ። በተቃራኒው፥ በየዕለት ጉዳያችን

ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ከሁሉ የላቀ ስፍራ የምንሰጠው ከሆነ ሕዝቡ በትጋታችን ጽናት ይማረካል። በተጨማሪ እኛን መቀበልና ማክበር ምናልባትም መውደድ ከተማሩ ከስብሰባ በመቅረት ሊያሳዝኑን አይፈልጉም።

ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ሰዎች ከፍተኛ መንፈሳዊ ጉድለት ለሚሟላት ስንል በተቻለ መጠን ሁልጊዜም ልናስተምራቸው ይገባል። በተጨማሪም፥ ያንን ስፍራ እንድንለቅ የሚያደርጉን ችግሮች ወይም ማናቸውም ነገሮች መቼ ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ፈጽሞ ስለማናውቅ ጊዜያችንን በሚገባ በመጠቀም ሕዝቡን የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ባለን ኃይል ሁሉ መሥራት አለብን። ፓላዋን በለቀቅን ጊዜ የተሰማኝን ኃዘን አልዘነጋውም፤ ነገር ግን በጌታ ጸጋ ቀንና ሌሊት የወንጌልን መልእክት ለሕዝቡ ለመስጠትና እውነትን ለአማኞች ለማስተማር በጊዜዬ ተግቼ ስለነበር ልቤ በምስጋና ሞልቶ ነበር። መሠራት ያለባቸው ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ነበሩ፤ ነገር ግን አውሮፕላኑ የነበርንበትን ጣቢያ ለቅቆ ሲበር ከታች በሽለቆው ውስጥ ተበታትነው ያሉትን ቤቶች ተመለከትሁና ጌታ በጸጋው የኢየሱስ ክርስቶስን የአምባሳደርነት ኃላፊነት እንድወጣ ስላደረገኝ አምልኮና ምስጋና አቀረብሁለት።

ከፓላዋኖዎች ጋር በምንኖርበት ጊዜ ለዘላለም አብረናቸው እንደማንዘልቅ ግልጽ ማድረጋችን እጅግ ጠቃሚ ሆኖ አግኝተነዋል። እኛ የወንጌል መልእክተኞች የመጣነው በዚያ ስፍራ ለእነዚያ ሰዎች እንደ ቋሚ አስተማሪ ወይም መጋቢ ለመሥራት አለመሆኑን በምንነግራቸው ወቅት በጥንቃቄ ልናደርገው ይገባል። ምክንያቱም ለአንዳንድ የአካባቢ ሰዎች ይህ ልባቸውን የሚሰብር ነው። በማስተማር አገልግሎታችን ገና ከመጀመሪያው ለፓላዋኖዎች በአትኩሮት ከነገርናቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፦ (1) በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር መልእክት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው፤ (2) እግዚአብሔር ወደ እናንተ የላከን ይህን መልእክት እንድንነግራችሁ ነው፤ (3) እግዚአብሔር ለእነርሱ እንድናስተምራቸው የሚፈልገው ነገር በርካታ እንደሆነና ይህን አስተምሮ ለመጨረስ ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅ፥ (4) እግዚአብሔር ይህን መልእክት እንድናደርስላቸው የሚፈልጋቸው ከእነርሱ ሌላ በርካታ ሰዎች መኖራቸውን፤ (5) ከእነርሱ ጋር የምንቆይበት ጊዜ ሦስት ዓመት ያህል እንደሚሆንና ከዚያ በኋላ ወደ ሌሎች እንደምንሄድ (6) ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ሁልጊዜ ጊዜን መስጠት እንዳለባቸው እንነግራቸው ነበር። በተደጋጋሚ እነዚህን ነጥቦች በማሳሰባችን የእግዚአብሔርን ቃል የመስማቱ አስፈላጊነት በእርግጥም ሁለንተናቸውን ወረሰው።

በነገራችን ላይ በአንድ ቦታ ብዙ ጊዜ ያለመቆየታችን እውነታ በአገልግሎታችን ለተቆረቆሩት አብያተ ክርስቲያናት ያለንን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ያቅበዋል ማለት አይደለም። ሐዋርያት የእምነት ልጆቻቸውን ከመንከባከብ አልታቀቡም ነበር። የተደራጁ አብያተ ክርስቲያናት ካሉበት ፓላዋን ለቀን ብንወጣም፥ አማኞችን ለማበረታታትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለመርዳትና ለማስተማር በየወሩ እንጐበኛቸው ነበር።

የወንጌል ስብሰባዎች ምን ዓይነት መሆን አለባቸው?

በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት የጀመርኸውን የውይይት ስልት ቀጥልበት። የአካባቢው ሰዎች ጥያቄዎችን የሚጠይቁና መልስ የሚሰጡ፥ በሚማሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ የሚወያዩና፥ በወንጌል ትምህርት ወቅት አስተያየታቸውን የሚሰጡ ከሆነ፥ ፍላጐታቸው ይጨምራል። ትምህርቱንም ዘና ብለው በፍጥነት የሚከታተሉ ሲሆን፥ ካመኑ በኋላም በአዲስ ኪዳን የአካል መመሪያዎች መሠረት ለመሥራት በሚገባ የተዘጋጁ ይሆናሉ።

አንዳንዶች በሌሎች እንቅስቃሴዎች፥ በዓይነ-አፋርነት ወይም በአእምሮ ዝግምተኛነት ምክንያት በሚገባ ለማዳመጥና ለማሳተፍ ባይችሉም የወንጌል መልእክተኛው ሊያበረታታቸው ይገባል።

እኔና ባለቤቴ ሴኔጋልን በምንጐበኝበት ወቅት ጆን ሚኪትሰን በቡዲክ ሕዝብ መካከል የወንጌል ስበሰባ ስለሚያካሂድ በዚያ አብረን እንድንሳተፍ ጠየቀን። ስብሰባው ይካሄድ የነበረው ሌሊት ከጭቃ ጡቦች ከተሠሩ ቤቶቻቸው ደጃፍ ነበር። ጆን መናገር በሚጀምርበት ጊዜ አንዳንድ ወጣት ሴቶች ጀርባቸውን ሰጥተውት ተቀመጡ። በሌላ ነገር ተጠምደው ስለነበር ማውራትና መሣሣቅ ጀመሩ። ጆን የሰዎቹን ፍላጐት ለማግኘትና ለመቆጣጠር እንዲሁም የሚያስተምራቸው ትምህርት ገብቶአቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ በርካታ ጥያቄዎች ይጠይቅ ነበር። በስብሰባው የነበሩ ወንዶችና ሴቶች መልስ በመስጠት ሲሳተፉ፥ እነዚህ ወጣት ሴቶች በራሳቸው ጉዳይ ተጠምደው ጆንን እስከናካቴው ረስተውት ነበር። በንግግራቸውና በሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ተይዘው ነበር። በመጨረሻ ጆን እነርሱንም ጥያቄ ጠየቃቸው። ወዲያውኑ ስላልሰሙት እንደገና ጠየቃቸው። በዚህ ጊዜ አንዳንዶች አካባቢያቸውን ይመለከቱ ጀመር። ጆን የሚፈልገውን ምላሽ ባያገኝ እንኳ ፈገግ ብሎ «ለመሆኑ በዚያ ምን እየሠራችሁ ነው?» ብሎ ጠየቃቸው። እነዚህ ሴቶች ልጆች ከመሣሣቅ በቀር አሁንም መልስ አልሰጡም። አያዳመጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በመፈለግ ጆን በቀጥታ በመንቀሳቀስ ወደነበሩበት ስፍራ ሄደ። ይህ የተቀሩትን ሰዎች ሁሉ አስገረማቸው። ሴቶቹ ልጆች ለቤተሰቦቻቸው እራት የሚሆን

የአትክልት ምግብ እያዘጋጁ መሆናቸውን ካየ በኋላ ሥራቸውን በጥንቃቄ ስለማከናወናቸው አመስግኖ፥ እየሠሩ እንዲያዳምጡ በማበረታታት ወደ ትምህርቱ ተመለሰ።

ሥልጣን የተሞላው የወንጌል ስርጭት

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል በማንበብ ተሳታፊዎች ስለዚያ ክፍል ያላቸውን አሳብ የሚሰጡበትና ከዚያም መሪው የተለያዩ አሳቦችንና አተረጓጐሞችን አሳጥሮ የሚያቀርብበት ዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ አለ። ሰዎችን አሳትፏቸው ስል ይህን ለማለት ግን አይደለም። ከእግዚአብሔር ቃል ሥልጣናዊ ምላሽ የማይሰጥ ትምህርት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ ባለሥልጣን አድርጐ ለማቅረብ እንጂ የሰዎችን ሕሊና ለራሱ ወይም እርሱ ለሚሰጠው ትርጉም ለማስገዛት የሚናገር መሆን የለበትም።

በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች ያላቸውን አመለካከት ለመለየት ሕዝቡን ጥያቄዎች ጠይቀሃል። በዋናው የወንጌል ስርጭት ወቅት ግን እንደ እነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መቀጠል የለባቸውም። ሰዎች የራሳቸውን ሃይማኖታዊ አመለካከቶችና እምነቶች በወንጌል ስብሰባዎች ላይ መግለጻቸውን ከቀጠሉ፥ የዚያ ስብሰባ ዓላማ እምነታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ማወዳደር ሳይሆን ለመንፈሳዊ እውነት ብቸኛ ተአማኒነት ያለውን ምንጭ ማለትም፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት እንደሆነ በትሕትና አስረዳቸው። ይህን ለማድረግ በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት ሌሎች ሰዎች፥ ነገዶችና ሃይማኖቶች ምን እንደሚያምኑ፥ መንፈሳዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በዓለም ውስጥ ስለሚታየው ውዥንብር፥ ለእነዚህም መልስ መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ስለመሆኑና ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማድረጉን አስታውሳቸው። ይህ ማሳሰቢያ የተሰበሰባችሁት እግዚአብሔር የሚናገረውን እንጂ እነርሱም ሆኑ ሌላ ማንኛውም ሰው እውነት ነው ብሎ የሚያስበውን ነገር ለመስማት እንዳልሆነ የተናገርነውን አሳብ ያጠናክርልናል።

በወንጌል ስርጭት ወቅት እነዚህን ሁሉ በአእምሮአችን ይዘን፥ ስለ ሕዝቡ ባህልና እምነት አዳዲስ ነገሮችን ለመማር ሁልጊዜ ንቁ መሆን አለብን ። ብዙ ጊዜ ሰዎች የቅዱሳት መጻሕፍት እውነት በሕይወታቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማምጣት እስኪጀምር ከፍት ሆነው እውነተኛ እምነታቸውን አይገልጡም። ይሁንና፥ ሰዎች ሁሉ አሳባቸውን ሙሉ ለሙሉ በነፃነት የሚገልጹበትን ሁኔታና ማንም

ሰው በሚናገረውና በሚያስበው ላይ ሳይመሠረት የእግዚአብሔርን እውነት ለማወጅ በሚችል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሚሰጥ አገልግሎት መካከል ያለውን ሚዛን ጠብቅ (1ኛ ተሰ. 1፡5፤ 2፡4፥5)።

መጽሐፍ ቅዱስ – ብቸኛው ባለሥልጣን

ለመንፈሳዊ ነገሮች ያለህ እውቀት በሙሉ የሚገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነና ባለሥልጣኑ አንተ እንዳይደለህ የምታተኩርበት አንዱ መንገድ በምታስተምርበት ጊዜ ሁሉ የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ ከፊትህ እንዳይለይ ማድረግ ነው። በዚያ አካባቢ ቋንቋ የተተረጐመ መጽሐፍ ቅዱስ ባይኖር እንኳ በብሔራዊ ቋንቋ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ከሕዝቡ ፊት ማድረግ በጣም ጥሩ ልምምድ ነው። በምታስተምርበት ጊዜ በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምታስተምረውን ክፍል አንብብ። ጣትህንም ከጥቅሱ ላይ አኑር።

በፓላዋኖዎች መካከል በምንሠራበት ጊዜ በግምት ሠላሳ ሰዎችና አንድ ወይም ሁለት ውሾች በትንሽ ደካማ የአካባቢው ቤት ተጣበን እንገኝ ነበር። ለመቀመጫ የሚሆን ቦታ እንኳ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር። በማነብበት ጊዜ ሰዎቹ ሁሉ ሊያዩኝ በሚችሉበት ሁኔታ ከአንድ ማዕዘን ጥግ ስቀመጥ፥ ሰዎቹ በሌላው ጥግ ተጣበው ይቀመጡ ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ በምጠቅስበት ጊዜ ትምህርቱ በሚሰጥበት ጥቅስ ላይ ጣቴን አሳርፍና አሳይ ነበር። ለብዙዎቹ አያት የሆኑ የዚያ ቡድን አለቃ አዛውንት ብዙ ጊዜ በእኔ አጠገብ ይቀመጡ ነበር። የማነበውን ጥቅስ በጣቴ በማሳይበት ጊዜ እኚህ አዛውንት ለማንበብ ባይችሉም እንኳ የማመለክተውን ሆን ብለው በአድናቆት ያዩ ነበር።

እግዚአብሔር በመፍሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይጽፍልን ኖሮ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች መልሶችን ለማወቅ እንደማልችል ያለማቋረጥ አሳስባቸው ነበር። በዚያ ሰዓት ሊመለስ የሚገባውን ጥያቄ ቢጠይቁኝ ለዚያ መልስ የሚሆን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ፈልጌ በማውጣት መልሱን ስሰጥ በጣቴ አመልክቼ አሳያቸዋለሁ። ለዚያ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው መልስ ከሌለ ያንኑ እነግራቸዋለሁ። አንዳንድ ጊዜ ከመካከላቸው አንዱ ጥያቄ ሲጠይቀኝ ሌላው «መልሱን አሁን ስለማያውቀው ከመጽሐፉ ቅዱስ መመልከት አለበት» በማለት ይመልስ ነበር።

ከወንጌል ስርጭት የመጀመሪያ ወቅት ጀምሮ ይህን ማድረግ ጥሩ ምሳሌ ነው። ከእነዚህ ሕዘቦች መካከል ሰዎች ዳግም ሲወለዱ በቃልና በተግባር ያሳየናቸውን ምሳሌ በመከተል ብቸኛው ባለሥልጣን ወደሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታሉ።

ልማዳዊ የወንጌል ስርጭት

ልማዳዊ የወንጌል ስርጭት ስብሰባዎች ጥቂት መዝሙሮችንና አዝማቾችን በመዘመር ይጀመሩና የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ጸሎት በተከታታይ ይደረጋል። ለስኬታማ የወንጌል ስብሰባ ብዙ ክርስቲያኖች እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች እንደሆኑ ቢያስቡም እንደዚህ ዓይነቱን የወንጌል ስብሰባ በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ክፍል አናገኝም። ይህ እንደእነዚህ ዓይነት ተግባራትን ከወዲሁ የሚኮንን አይደለም። ነገር ግን የወንጌል ስርጭት ዘዴዎቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ የታዘዝናቸው፥ ከጌታ ኢየሱስ ወይም ከሐዋርያት ምሳሌነት የተከተልናቸው እንዳይደሉ እውነት ነው። በተለምዶ ብቻ የምናደርጋቸው ናቸው። በተለምዶ የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የግድ ስሕተት ናቸው ማለት አይደለም፤ ይሁንና ጠቃሚዎች ወይም ጎጂዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል። ብዙውን ጊዜ ተለምዶአዊ የወንጌል ስርጭት መንገዶች ባልዳኑ ሰዎች አእምሮ የተሳሳተ ግንዛቤና መደናገር ይፈጥራሉ።

ሥርዓቶችና ወጎች ሙት ሃይማኖቶች አጥብቀው የሚይዟቸው ሃይማኖታዊ ተግባራት ናቸው። የገጠር ሰዎች የእምላኮቻቸውን ወይም የመናፍስቶችን ቁጣ ለማብረድ፥ ሞገስን ለማግኘት፥ ሀብትን ለማካበትና ጤንነትን ለመጠበቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ወጎች ወሳኝ መንገዶች እንደሆኑ ያምናሉ። ብዙ የወንጌል መልእክተኞች የወንጌል ስብሰባዎችን በሚያካሄዱበት ወቅት ለሥርዓቶች የሚሰጡት ስፍራ እጅግ አነስተኛ ስለሆነ፥ ሕዝቡ የወንጌል ስርጭት የማካሄጃ ዘዴዎችን ለክርስትና የግድ የሚያስፈልጉና አንድ ሰው የክርስቲያን አምላክን ለማስደሰት የሚፈጽማቸው ነገሮች ናቸው ብሎ ሊተረጉም እንደሚችል አይገነዘቡም። ይህም ሆኖ፥ እያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ ሃይማኖታዊ ፋይዳ በሚሰጥበትና የባዕድ አምልኮ በገነነበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች፥ ተለምዶአዊ የወንጌል ማሰራጫ ማቅረቢያ ዘዴዎችን የሚተረጉሙት በዚህ መንገድ ነው።

የወንጌል መልእክተኛው መዝሙር ሲያዘምር አሳቡ ያለው ወዳልዳኑት በሚተላለፈው የመዝሙር መልእክት ላይ ነው። በሚጸልይበት ጊዜ በፊት ለፊቱ የተከማቹት ሰዎች ስለሚያጡት ነገር በማሰብ የእግዚአብሔር ኃይል እንዲወቅሳቸውና ነፍሳቸውን እንዲያድን ይማልዳል። ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚያስተምርበት ጊዜ እምነቱ ሰዎችን ወደ ደኅንነት ሊያመጣ በሚችል በእግዚአብሔር ቃል ኃይልና እውነት ላይ ነው። ከእነዚህ ተግባራት የትኞቹም በእግዚአብሔር ዘንድ ችሮታን ለማግኘት የሚፈጸሙ አይደሉም። ነገር ግን ሕይወታቸውን ሙሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ችሮታን ለማግኘት የተደጋገሙ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ሲገነቡ ለኖሩ ሰዎች ይህን መረዳት አስቸጋሪ

ነው። ኃጢአተኛው ሰው ቅዱሱን አምላክ ደስ የማሰኘት ብቃት እንደሌለው ስለማያውቁ፥ የወንጌል መልእክተኛው በወንጌል ስብሰባ ወቅት የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ከእነርሱ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል የእግዚአብሔርን ችሮታ የማግኘያ መንገድ አድርገው ሊተረጉሙት ይችላሉ። የተመረጡት መዝሙሮችና አዝማቾች ወንጌልን ሊያስተላልፉ ቢችሉም፥ በመዘመር ሰዎቹ እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኙ ማሰባቸው በመዝሙሮቹ ከሚማሯቸው ማናቸውም እውነቶች ይልቃል። ሰዎቹ የወንጌል ስብሰባዎችን በሚካፈሉበት ጊዜ የሚያደርጉአቸው ነገሮች ሁሉ ለደኅንነታቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እንደሌለ የወንጌል መልእክተኛው ቢናገርም እንኳ፥ ብዙ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ መረዳታቸው አይቀርም።

እንደ ሌሎቹ የሰው ልጆች ሃይማኖቶች ሁሉ የቡድሃ ሃይማኖትም የተመሠረተው የአምላክን ችሮታ ለማግኘት በሚሠራ ሰናይ ምግባር ላይ ነው። አንድ የወንጌል መልዕክተኛ ወደ ታይላንድ በሚጓዝበት ወቅት በአጠገቡ ለነበረ አንድ የቡድሃ ሃይማኖት ተከታይ መመስከር ጀመረ። የታይላንዱ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ለመስማት ፍላጐትና ፈቃደኝነት ስላሳየ የወንጌል መልእክተኛው ለረጅም ጊዜ ተናገረ። የወንጌል መልእክተኛው ንግግሩን ሲያጠቃልል ሰውዬው እንዲህ አለው፦ «ለእኔ ከሁሉ የላቀ አስደናቂ የሆነልኝ ነገር የልጄ የቡድሃ ሃይማኖት ካህን መሆን ነው»

ይህ የቡድሃ እምነት ተከታይ የወንጌል መልእክተኛውን በትዕግሥትና በጉጉት ያዳመጠው ለምን ነበር? በሚሰማው ነገር ደስ ተሰኝቶ ነበርን? አልነበረም! ያዳመጠው ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለወንጌል መልእክተኛው ጥቅም ነበር። ሰውየው ከዚህ ቀደም ባደረጋቸው ተግባራትና ልጁ የቡድሃ ሃይማኖት ካህን በመሆኑ የአምላክን ችሮታ እንዳገኘ ስለሚያስብ፥ የወንጌል መልእክተኛውም ስለ ክርስቲያን አምላኩ ብዙ በመናገሩ ችሮታ የሚያገኝ መስሎት ነበር። ታይላንዳዊው የወንጌል መልእክተኛውን ጥረት የተረጐመው ማናቸውም የምናደርጋቸው መልካም ነገሮች ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናገኘውን የግል ችሮታ ያሳድጉልናል በሚለው የቡድሃ ሃይማኖት አስተሳሰብ ነበር።

ደኅንነት በሥራ እንደሚገኝ ተደርጐ የተሳሳተ ወንጌል በሚሰበኩባቸው ስፍራዎች ተለምዶአዊውን የወንጌል ስብሰባ ብዙ ጊዜ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል። ሰዎች ክርስቲያን መሆንን ቤተ ክርስቲያን ከመሄድና በሃይማኖታዊ ተግባራት ከመሳተፍ ጋር ስለሚያዛምዱት፥ ወደ ወንጌል ስብሰባዎች መሄድ ክርስቲያን ለመሆን እንደሚረዳቸው ያስባሉ። የወንጌል ስብሰባ የተሳሳተ ሃይማኖታዊ ድባብ ይፈጥራል። በመሆኑም፥ ብዙ ሰዎች የወንጌል መልእክተኞች ወይም የአንድ

የእምነት ክፍልን ስብሰባ በመካፈላቸው ክርስቲያኖች የሆኑ ይመስላቸዋል። ስለዚህ ሰዎች «የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ እየተካፈሉ» እንደሆነ እንዳይሰማቸው ማድረግ ያሻል። የቅድመ-ወንጌል የጉብኝት ጊዜያትን እንዳካሄድህ፥ የማይነቃነቅ ሥርዓትን ባልተከተለ መልክ የወንጌል ስብሰባዎችንም አድርግ።

አንዳንድ የወንጌል መልእክተኞች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጣቸውን በቀጠሉ ቁጥር በመጨረሻ እውነቱን ይረዱና ይድናሉ ብለው ስለሚገምቱ፥ ይህንን ጉዳይ እንደ ችግር ላይመለከቱ ይችላሉ። አንዳንዶች በዚህ መንገድ መዳናቸው እውነት ቢሆንም እንኳ ሌሎች ብዙዎች ግን «ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው» የውሸት ዋስትና ያገኙና የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛ መልእክት ለመቀበል ከፍት አእምሮ ሳይኖራቸው ይቀራሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠው በውሸት ራሳቸውን «ክርስቲያን» ብለው የሚጠሩ በርካታ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያን ከማዘውተራቸው የተነሣ እንደ ተቀበላቸው በማሰብ መታለላቸው ሁሉም የክርስትና አገልግሎት ተካፋዮች የሚያውቁት ነው። እኛ ሚሊዮናውያን ሁላችን የወንጌል ስብከት ዘዴዎቻችንን በጥንቃቄ በመመርመር፥ ይበልጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚመሠረቱትንና የተሳሳተ ግንዛቤ በመፍጠር ሰይጣን «ድኛለሁ» የሚሉትን ወገኖች በቀላሉ ለማታለል እንዳይችል የሚያግዙትን አማራጭ ስልቶች በመጠቀም ከውሸት የደኅንነት ዋስትና የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን።

በፓፑዋ ኒው ጊኒ የሚሠራ አንድ የወንጌል መልእክተኛ የወንጌል መልእክተኞች ሁሉ በወንጌል መልእክታቸውና ዘዴዎቻቸው ንቁና ጥንቁቅ መሆን እንደሚያስፈልጋቸው ለማሳየት የሚከተለውን ጽፏል፦

«የወንጌል መልእክተኛው እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላና በኃጢአት ላይ እንድሚፈርድ በሚያስተምሩበት ጊዜ እንኳ ምላሹ ‹ምን ማድረግ ይገባኛል? ምን ልስጥ?› የሚል ነው። በብዙ ሕዝቦች ዘንድ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች የተለመዱ በመሆናቸው፥ የወንጌል መልእክተኛው አዲስ መልእክት በአካባቢው ሰዎች እእምሮ አዲስን ሥርዓት የሚጋብዝ ነው። ራሳቸውን የመታጠብ ሥርዓት (ጥምቀት)፥ የአያት ቅድማያቶቻቸውን ሥጋ የመብላትና ደማቸውን የመጠጣት ሥርዓት (ቅዱስ ቁርባን)፥ ገንዘብ የመስጠት (መባ)፥ አዲስ መዝሙር የመዘመርና ‹የቤተ ክርስቲያን ንግግሮችን› የማድመጥ ሥርዓት ይለግመዳሉ። ስለዚህ ‹ልናደርጋቸው የሚገቡ ሥርዓቶች እነዚህ ናቸው› ብለው ያስባሉ። ከጥቂቱ መጽሐፍ ማንበብ መማር አለብን ይላሉ። በፓፑዋ ኒው

ጊኒ የእሑድ ስብሰባዎች ልማዳዊ በሆኑ የቤተ ክርስቲያን ተግባራት መጀመር እጅግ ቀላል ነው። ይህ ግን ዓላማችን አይደለም።

«በፓፑዋ ኒው ጊኒ ሌላ ያየሁት አደገኛ ነገር ቁሳዊ ብልጽግናን ለማግኘት አንዳንድ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች መፈጸም ያስፈልጋል የሚል ዝንባሌ ነበር። የወንጌል መልእክተኛው ካለው ሀብት በመነሣት ቁሳዊ ሀብት የሚገኝበትን ምሥጢር ያውቃል። ምሥጢሩ ያለው በሃይማኖቱ በተለይ ደግሞ በሥርዓቶቹ ነው የሚል ነበር። በእነርሱ አስተሳሰብ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ አሁንም ቢሆን የወንጌል መልእክተኛው ይዞአቸው የመጣውን ዓይነት ነገሮች ማለትም ልብሶችን፥ ሬዲዮዎችን፥ የታሸጉ ምግቦችን፥ መኪናዎች፥ ወዘተ በመሥራት ላይ ይገኛል።

«ይህ የሚያሳየን ወንጌልን በጥንቃቄ ማቅረብ እንደሚጠበቅብን ነው። ምንም ነገር የምንገምተው ካለ ሰዎች መልእክታችንን ተረድተውታል ከምንል ይልቅ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ይሆናል ብለን መጠበቅ አለብን።»

ሰው ሠራሽ ሃይማኖታዊ ድባብ አትፍጠሩ

መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀመው እውነትን ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ኃይልና ሥራ በሰው– ሠራሽ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ሁኔታ የሚወሰን አይደለም። ኢየሱስና ሐዋርያት የእግዚአብሔርን እውነት በተለምዶአዊና ዕለታዊ ሁኔታዎች ይናገሩ ነበር። በሚናገሩት የእውነት መልእክት ውስጥ ባለ ኃይል ብቻ በመደገፋቸው፥ ሰው ሠራሽ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሰዎች እግዚአብሔር እንዳለ እንዲሰማቸው አያደርጉም ነበር። ጳውሎስ ለቄላስይስ አማኞች ወንጌል ወደ እነርሱ የመጣው እንዴት እንደነበር ሲናገር፥ «ይህም በዓለም ሁሉ እንዳለ ወደ እናንተ ደርሶአል የእግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት ከሰማችሁበትና ካወቃችሁበት ቀን ጀምሮ በእናንተ ደግሞ እንዳለ በዓለም ፍሬ ያፈራል ያድግማል» ብሏል (ቈላ. 1፡6)

በፓላዋን እያለሁ አንድ እጅግ ኃይለኛ የሆነ ጠንቋይ አሸምቆ ሊገድለኝ እንዳቀደ ከበርካታ ምንጮች ሰማሁ። ስለዚህ አንድ ቀን በመንገድ ላይ ሳያስደነግጠኝ ፊት ለፊት በሕዝቡ ፊት ብገጥመው መልካም ይሆናል ብዬ ወሰንሁ። በተገናኘንበት ወቅት መጀመሪያ ፍርሃትና ኃፍረት ያሸማቀቀው ቢመስልም፥ ቆይቶ ዝምተኛና ተግባቢ ሆኖ ተገኘ። ሊገድለኝ አሳብ እንዳለው ፊት ለፊት ስጠይቀው ሙሉ በሙሉ ካደ።

ለሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ንግግሬን ከእርሱ ጋር በመቀጠል ጥያቄዎችን እጠይቅ ጀመር። ነገር ግን ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶች ወይም የግል አስተያየቶቼን አልሰጠሁትም (ልክ በቅድመ-ወንጌል ወቅት እንደሚሆነው)። ከተፈጥሮ፥ ከማይታዩ መንፈሳዊ ኃይላት፥ ከሰውና ከሞት በኋላ ካለው ሕይወት ጋር ስለተያያዙ በርካታ ጉዳዮች ጠየቅሁት፤ በመጨረሻም፥ መጽሐፍ ቅዱስን አንስቼ እርሱ ግልጽ የሆኑ መልሶች ሊሰጥ ያልቻለባቸውን ጥያቄዎች የሚመልስ የእግዚአብሔር መገለጥ ያለበት መጽሐፍ እንደሆነ አስተዋወቅሁት።

ለጠየቅሁት አስቸጋሪ ጥያቄዎች በሙሉ መልሶችን የያዘ ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ መጽሐፍ እንዳለኝ ተገንዝቦ እንደ መደነቅ አለ። ከዚህ በኋላ ነበር፥ «ተከታዮቼ ሁሉ እንዲከተሉህ እነግራቸዋለሁ» የሚል አስደናቂ ቃል የተናገረው።

ወዲያውኑ፥ «እንድታደርግ የምፈልገው ያንን አይደለም» ስለው ይበልጥ ተደነቀ። በመቀጠል፥ «አሁን አንተን ይከተሉሃል፤ ሆኖም አንተ አምላክ አይደለህም። እኔም አምላክ ስላይደለሁ እኔን መከተላቸው ምንም አይጠቅምም።

በመልሴ በመገረም፥ «ታዲያ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?» በማለት ጠየቀኝ።

«ወደ ፓላዋን ደሴት የመጣሁት ሰዎች እንዲከተሉኝ ሳይሆን ፓላዋኖዎች በሙሉ ይህን በእግዚአብሔር የተጻፈውን መልእክት እንዲያውቁ ነው። እግዚአብሔር እንድታውቁት የሚፈልገውን ነገር በሙሉ ልነግራችሁ ብቻ እፈልጋለሁ። ስለዚህ ሕዝቡን በቤትህ ሰብስበህ የእግዚአብሔርን መልእክት በጥንቃቄ እንድገልጽላቸው ፍቀድልኝ» አልሁት።

በጥርጣሬ እየተመለከተኝ፥ «የምትፈልገው ይህንን ብቻ ነውን?» ሲል ጠየቀኝ።

«አዎን የምፈልገው ይህንን ብቻ ነው ። ከዚህ ሌላ ምንም እንድታደርግልኝ አልፈልግም። የእግዚአብሔርን ቃል እየሰማችሁ ልታጨሱ፥ ጫታችሁን ልትቅሙ፥ የዓሣ ማጥመጃ መረቦቻችሁን ልትጠግኑ፥ ቅርጫቶችን ልትሠሩ፥ ጠመንጃዎቻችሁን ልታበጁ ወይም የፈለጋችሁትን ነገር ልታደርጉ ትችላላችሁ። በማለት አረጋገጥኩለት።

በማጨሱና ጫት በመቃሙ ላይ ያተኮርሁበት ምክንያት አንዳንድ የወንጌል መልእክተኞችን ጨምሮ ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት እየተሰጠ ማጨስና መቃም እግዚአብሔርን ያስቀይመዋል የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ስለነበራቸው ነው። ስለዚህ

ለብሰባዎች እየተካሄዱ እንዳይፈጸሙ እንደነዚህ ዓይነት ተግባራት ይከለክሉ ነበር። ይህን የሚያደርጉት ላልዳኑ ሰዎች የሚደረጉ ስብሰባዎች የሚካሄዱት እግዚአብሔርን ለማምለክ የተለየ ቦታ ነው በሚባለው በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ስለሆነ ነው። የወንጌል ስብሰባዎች በቤት ወይም በሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች በተሻለ ሁኔታ ይካሄዳሉ ያልነው ለዚህ ነው። ምክንያቱም የማያምኑ ሰዎች ክርስቲያናዊ መለኪያና ተግባር የሚጠይቀውን ነገር እንዲያደርጉ ቦታው አያስገድዳቸውም። የወንጌል መልእክተኞች የእግዚአብሔርን መልእክት ላልዳኑት ሰዎች መስጠት የሚገባቸው በሕዝባዊ ስብሰባዎች የተለመደ ባህላዊ ድባብ ውስጥ ነው። በሌላ በኩል፥ የወንጌል መልእክተኞች ሰዎች በአግዳሚ ወንበሮች እንዲቀመጡ፥ እንዲዘምሩ፥ እንዲቆሙና እንዲቀመጡ፥ ለጸሎት ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ፥ ጥያቄ ወይም አሳብ ሳይሰጡ በዝምታ እንዲቆዩና በወንጌላት ወይም በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች እንደተገቢ ባሕርያት አድርገን የምንወስዳቸውን ነገሮች እንዲያደርጉና እንዳያደርጉ በመጠየቅ «ክርስቲያናዊ» ዐውድ ለመፍጠር መጣር የለባቸውም።

ያልዳኑ ሰዎችን በጸሎት መምራት

በብዙ የወንጌል ስብሰባዎች እንደተለመደው አንድ ሰው በጸሎት ይመራል። ይህ ያመኑ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር በሚያደርጉት ጸሎት ያላመኑትንም እንደማሳተፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። «የኃጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው። የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው (ምሳ. 15፡8)።

«ሕግን ከመስማት ጆሮውን የሚመልስ ጸሎቱ አስጸያፊ ናት» (ምሳሌ 28፡9) ኢየሱስና ሐዋርያት የወንጌልን ሥራ ሲሠሩ አንድም ቀን ካላመኑ (ካልዳኑ) ሰዎች ጋር ስለመጸለያቸው የተጻፈ ነገር የለም።

ጌታ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡– «...በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ. 14፡6)። ጸሎት በኢየሱስ ስም መደረግ አለበት። አማኞች በሚጸልዩበት ጊዜ፥ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም ይገባሉ (ዕብ. 10፡19)። የማያምኑ ሰዎች በኢየሱስ ስም ወደ እግዚአብሔር መምጣት አይችሉም። የእግዚአብሔርም ልጆች የሰይጣንን ልጆች ከእነርሱ ጋር ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሕልውና ሊያስገቡ አይችሉም። የማያምኑ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ ለመግባት እንደማይችሉ በክርስቶስና በሞቱ ብቻ የኃጢአታቸውን ይቅርታ አግኝተው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚታረቁ መማር አላባቸው። እምነው ከመታረቃቸው በፊት እንዴት አብረውን እንዲጸልዩ እንጋብዛቸዋለን?

ብዙ ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት ሰይጣን ያልዳኑ ሰዎች እንደዳኑና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙ እንዲመስላቸው ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ነው። የማያምኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት የመገኘታቸው ጉዳይ ጨርሶ የማይቻል ሆኖ ሳለ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች የማያምኑ ሰዎችን ከመዳናቸው በፊት እንዲጸልዩ ያበረታቱአቸዋል ወይም ያስተምሩአቸዋል። ይህም ሰዎች እውነተኛ ንስሐ እንዳይገቡ በመከልከል፥ ክርስቶስ በእነርሱ ምትክ ያደረገውን የማዳን ሥራ እንዳይቀበሉ ያግዳቸዋል።

የዚህን ጉዳይ ከባድነት ያልተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ይህ የጸጉር ስንጠቃ እንደሆነ ሊገምቱ ይችላሉ። ነገር ግን በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የተደራጁ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሐሰተኛ ዋስትና የሚሰማቸው ሰዎች እንዳሉ የተገነዘቡ ወገኖች፥ ይህን ጉዳይ በጥንቃቄ ልንመለከተው እንደሚገባ ይስማማሉ። ሰይጣን ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙ እንዲሰማቸው በማድረግ ከደኅንነት ጠፍተው ያሉበትን እውነተኛ ሁኔታ እንዳይመለከቱ የሚጠቀምባቸው ማናቸውም የክርስቲያናዊ አገልግሎት መንገዶች ከወንጌል ስርጭት ዘዴዎች መወገድ አለባቸው።

አንዳንድ የፓላዋኖ ወጣቶች ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናታቸው በመነሣት ያልዳኑ ሰዎች ለሚገኙበት መንደር ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። እነዚህ ወጣት ወንጌላውያን በመንደሩ ሰዎች በየሳምንቱ መልካም አቀባበል ይደረግላቸው ነበር። ሰዎቹም መዝሙሮችን በደስታ ይዘምሩ፥ በጸሎትና ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚደረግ ንባብ በደስታ ይተባበሩ ነበር። የወንጌል መልእክቶችን በጥሩ አእምሮ በንቃት ቢከታተሉም፥ የንስሐ ምልክት ግን አያሳዩም ነበር። የደኅንነታቸው ተስፋ በክርስቶስ ላይ ያለ እምነት መሆኑን አፍ አውጥቶ የተናገረ አንድም ሰው አልነበረም።

እነዚህ ወጣት የወንጌል መልእክተኞች ምን ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም ነበር። እነዚህ ያልዳኑ ሰዎች ደስተኛና ዋስትና ያላቸው ይመስሉ ነበር። ማየት የቻሉ ስለሚመስላቸው፥ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው መንፈሳዊ ብርሃን እንድሚያስፈልጋቸው እንዳያዩ ታውረው ነበር (ዮሐ. 9፡40፥41)። ራሳቸውን «በእግዚአብሔር ውስጥ» እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሩ ነበር (በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጠውን ቃል በፓላዋን የነበሩ ያልዳኑ ሃይማኖተኞች ሁልጊዜ ይጠቀሙበት ነበር።)

አንድ ቀን እነዚህን ለብለባዎች ከሚያካሂዱት ወጣቶች መካከል ጥቂቶቹ በዚህ ጉዳይ ምክር እንድሰጣቸው ጠየቁኝ። አብዛኛዎቹ ሰዎች በመዘመራቸውና በመጸለያቸው ምክንያት እግዚአብሔር

እንደሚቀበላቸው እንደሚያስቡ ስለማውቅ፥ በስብሰባዎቹ መዝሙርና ጸሎት ማድረግን እንዲያቆሙ ነገርኋቸው።

እነዚህ ወጣቶች የሰጠሁትን ምክር በመጀመሪያ ሲሰሙ እጅግ ግራ ተጋቡ። ከእነዚህ ተግባራት ውጭ ስብሰባዎችን እንዴት ማካሄድ እንደሚችሉ ገረማቸው። ከዚህ ቀደም የተካፈሏቸው የወንጌል ስብሰባዎች በሙሉ በወንጌል መልእክተኞች እንደተዋቀረው መዝሙርንና ጸሎትን ያካተቱ ነበሩ። የእነርሱ ኃላፊነት የእግዚአብሔርን ቃል ላልዳኑ ሰዎች ማስተማር ብቻ እንደሆነና መዝሙርና ጸሎት መካተት ያለበት በእግዚአብሔር ልጆች ስብሰባ ብቻ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ አስረዳኋቸው። «ሕዝቡን ሰብስቡና የእግዚአብሔርን ቃል አስተምሩት። ኢየሱስና ሐዋርያት ያደረጉት ይህንኑ ነበር። ሕዝቡ መዝሙር እንዲዘምርና እንዲጸልይ በቅድሚያ አትጠይቁት» አልኋቸው።

በተጨማሪም፥ ለጊዜው የወንጌል ሰበካውን ተግባር እንዲያቆሙ መከርኋቸው። «የምታስተምሯቸው ያልዳኑ ሰዎች ወንጌልን ብዙ ጊዜያት ሰምተዋል። ግን ምንም አልጠቀማቸውም። መዘመራቸው፥ መጸለያቸውና መልእክቱን መስማታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ስላስመሰላቸው በዚህ ፈጽሞ ረክተዋል። በእዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ሊማሩ የሚገባቸው የእግዚአብሔርን ቅድስና፥ ሕጉ ኃጢአተኞች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ከፈለጉ ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግና እነርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃሎች በሙላት ለመታዘዝ ያለመቻላቸውንና ኃጢአተኞች መሆናቸውን ነው። በዚህ መንገድ ካልተዘጋጁ በስተቀር ጌታ ኢየሱስና ወንጌል እንደሚያስፈልጋቸው ለማየት አይችሉም» ስል አስረዳኋቸው።

ከዚሁ ውይይት በኋላ፥ ወጣቶች ከስብሰባዎቻቸው መዝሙርንና ጸሎትን ለምን ማስቀረት እንዳለባቸው ተረዱ። በሚቀጥለው ጊዜ ወደዚያ መንደር ሲሄዱ ሆን ብለው የመዝሙር መጽሐፎቻቸውን ሳይዙ ሄዱ። ከሕዝቡ ጋር ሲገናኙም የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ቅድስናና ጽድቅ ላይ አተኩረው ማስተማራቸውን ቀጠሉ፤ በዚህም እያንዳንዱ ሰው ንስሐ መግባት እንዳለበት፥ ማለትም ኃጢአተኞች እንደሆኑና በፍትሐዊ ፍርድ መኮነናቸውን እንዲያምኑ ገለጹላቸው።

እነዚህ ወጣቶች ልክ ማስተማር ሲጀምሩ፥ አንዳንድ ሰዎች እያቋረጧቸው «መዘመርና መጸለይ የለም እንዴ?» ይሉ ነበር።

ወጣቶቹም፥ «አዎን አንዘምርም አንጸልይም» ሲሉ መለሱላቸው። ከዚያም በወንጌል ስብሰባዎቻቸው ውስጥ መጸለይና መዘመር ማቆም ለምን እንዳስፈለገ ገለጡላቸው። እንዲህም አሏቸው፦ «እግዚአብሔር

የሰይጣንን ልጆች ስለ እርሱ እንዲዘምሩ በፍጹም ጠይቆአቸው አያውቅም። እግዚአብሔር የእርሱ ልጆች ያልሆኑ ሰዎች የሚዘምሩትን መዝሙር አይቀበልም። ለእርሱ ምስጋና ይሆን ዘንድ እንዲዘምሩ የሚጠይቀው ልጆቹን ብቻ ነው» አሏቸው (ኤፌሶን 5፡18-20 ተመልከት)።

በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል ኃጢአት ስላለ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንድትጸልዩ አይጠይቃችሁም፤ ወደ እግዚአብሔር ልትመጡና ከእርሱ ጋር ልትነጋገሩ አትችሉም። (ኢሳ. 59፡1፥2፤ ኤፌ. 2፡11-13 ተመልከት።) ወደ እናንተ ለመምጣት ከመንደሮቻችን ከመነሣታችን በፊት እኛና በመንደሮቻችን ያሉ አማኞች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ፈጽሞ የማትችሉ ኃጢአተኞች መሆናችሁን እንድትገነዘቡ ጸሎት አድርገንላችኋል።

እነዚህ ያልዳኑ ሰዎች ለዚህ ያቀረቡት ጥያቄ፥ «ታዲያ እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው?» የሚል ነበር።

የተሰጣቸው መልስ፥ «የእግዚአብሔርን ቃል በማድመጥ እርሱ በቃሉ ምን እንደሚላችሁ ማድረግ ብቻ ነው» የሚል ነበር።

የዚህ ልዩ አቀራረብ ውጤት ምን ነበር? ሕዝቡ ቀደም ብለው የተደገፉበትን ሃይማኖታዊ ተግባራት ስለተገፈፉ፥ በእግዚአብሔር ፊት ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ወደ መገንዘብ መጡ።

የአረማዊ እምነቶቻቸውንና የሰይጣን አምልኮአቸውን ለመተው ፈቃደኞች ያልሆኑ በርካታ ፓላዋኖዎች የክርስትና ውጫዊ ገጽታ የሆኑትን ነገሮች ለመለማመድ ዝግጁ ነበሩ። ምክንያቱም መዘመር፥ መጸለይና ስብሰባ መካፈል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል ብለው ያምኑ ነበር። አንድ ፓላዋኖአዊ ጠንቋይ ጥንቆላውንም ሳያቆም ተለምዶአዊውን የወንጌል ስብሰባ በመካፈል መዘመርና መጸለዩን ለረጅም ጊዜ ቀጥሎ ነበር። በጉረቤቱ ለነበሩ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አስተምሬ በጐጆው በኩል ሳልፍ፥ እዚያ ከመድረሳችን ብዙ ዓመታት በፊት የሰማቸውን መዝሙሮች ሲዘምር እሰማው ነበር።

ክርስቲያኖች ወደ ዓለም የተላክነው ከሃይማኖት ሥርዓት ጋር ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ቃል መልእክት ጋር ነበር። «... በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)፤ የሚያስፈልገን ይህ ብቻ ነው። የወንጌል ስርጭት ምሳሌዎቻችን ኢየሱስና ሐዋርያት ሊሆኑ ይገባል። ትኩረታቸው በእግዚአብሔር ቃል የሆነ አማኞች ሁሉ በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች ይህንኑ ቃል ለመስበክ ያለባቸው ኃላፊነት ነበር (2ኛ

ቆሮ. 4:1-7)። ከዚህ በቀር ምንም ስለማያስፈልግ እግዚአብሔር ሌላ ምንም አልሰጠም።

በቡድን ማስተማር

በአንድ የወንጌል ጣቢያ የሚሠራ ቡድን ባልና ሚስት፥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ያላገቡ ሰዎች ወይም በርካታ ባልና ሚስት ሊሆኑ ይችላሉ። የቡድኑ አባላት እነማንም ይሁኑ፥ እያንዳንዱን ትምህርት ለማስተማር በቡድን መሥራት እጅግ ውጤታማ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ነው።

አንድ ሙሉ ትምህርት ለማስተማር ችሎታው የሌላቸው ሰዎች እንኳ በቡድን ማስተማር ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ። ገና ቋንቋውን በሚገባ ለማይናገሩ አዳዲስ የወንጌል መልእክተኞች ወይም ለማስተማር ተግባር አዲስ ለሆኑና ምናልባትም ለሚፈሩና የማስተማር ልምድ ለሌላቸው የአካባቢ አማኞች የትምህርቱን አነስተኛ ክፍል መስጠቱ መልካም ይመስለኛል። ጥያቄዎችን አንዲጠይቁ የሕዝቡን ምላሾችና አስተያየቶች እንዲያጤኑ፥ ከአጽንዖት አለቅጥ መብዛት፥ የግብረሪያ ግነስ ወይም ከሌላ ከማንኛውም የጓደኞቹው የማስተማሪያ ዘዴ ድከመት ወይም የትምህርት ይዘት የተነሣ በአድማጮቹ ላይ ሊከሰት የሚችለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ወይም የተሳሳተ ትርጓሜ እንዲከታተሉ ማድረግ ይቻላል።

የወንጌል መልእክተኞች በቡድን በሚሠለጥኑበት ቦታ ትምህርቶች ከመቅረባቸው በፊት በቡድኑ አባላት በሙሉ ቢገመገሙ መልካም ነው። ይህ በአንድነት የመሥራትን መንፈስ ከማዳበሩ ባሻገር እያንዳንዱ የቡድን አባል ለትምህርቱ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ያግዛል። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የሚያስተምረው ቡድኑን በመወከል መሆኑንና አብሮአቸው ለሚሠሩ ሠራተኞች ምሪትና ለሚሰጡት ገንቢ አሳቦች ልቡ የተከፈተ መሆን አለበት።

> ብዙ ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማስተማር የሚችሉ ሰዎች በአንድነት ከሆኑ ተቀዳሚ የማስተማር ሥራውን ሊሠሩት ይችላሉ። በፓፑዋ ኒው ጊኒ በቢሥሪዮ ነገድ መካከል ይሠሩ የነበሩት ጆርጅ ፎከርና ቦብ ኪነል ስለ ማስተማሪያ መንገዳቸው የሚከተለውን ብለዋል፦
>
> «አገልግሎታችን ተደራራቢ ቢሆንም እንኳ፥ ባብዛኛው እኔ (ጆርጅ) የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሳዘጋጅ ቦብ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉምን ይሠራ ነበር። ከዚያም በየተራ እናስተምራለን። ቦብ በትርጉም አካባቢ ጫና ሲበዛበት እኔ ሁለት እርሱ አንድ ትምህርት በማፈራረቅ እናስተምራለን። ከዚያ እኔ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማዘጋጀት ሥራዬን እንድቀጥል እርሱ ሁለት እኔ አንድ የማስተምርበት ተራ ደግሞ ይመቻቻል።

«እኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በመጠቀም ከተተረጐመው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አስተምራለሁ። እኔ ቆሜ በማስተምርበት ጊዜ ቦብ ደግሞ መጻፊያ ደብተርና እርሳስ ይዞ በጉባኤው መካከል በመቀመጥ በትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ነጥቦች ሁሉ ማንሣቱን ለማረጋገጥ ማስታወሻ ይወስዳል። ከሰዎቹ ፊት የሚነበበውን የለሚት ገላጭ ለውጦች ይከታተላል። ። የሚሰጡትን አሳብ ይመዘግባል። ትምህርቱን እንደጨረስሁ ቦብ ይነግና በግሎት አሥር ደቂቃ ያህል የትምህርቱን ዋና ዋና አሳቦቹ ይከልሳል። ሰዎቹም በሰነዘሩት አሳብ ላይ አስተያየት ይሰጣል። ይህን ሲያደርግ ‹እዚያ ጋ ያላችሁት ነገር መልካም ነው... ነገር ግን እንደዚያ አልነበረም። እነደዚህ ማለት እንጂ...አሁን ሁላችሁም... አስተውሉ።› ሁልጊዜ በተደጋጋሚ ያለመረዳት ጭጋግ ስፍራውን እንዲለቅ እናደርጋለን። ቦብ በሚያስተምርበት ጊዜ እኔ የመከታተሉንና የመከለሱን ሥራ እሠራለሁ። ይህንን ፈጣን የክለሳ ሥራ ስንሠራ ትምህርቱ ከማለቁና በአእምሮአቸው ከመቀረጹ በፊት ወዲያውኑ ባሉበት ችግራቸውን እናቃልላለን።

«በአድማጮቹ መካከል በምንቀመጥበት ጊዜ የሚሰሙት ሰዎች የሚያስፈልገውን ነጥብ እንዳልያዙ ወይም ትምህርቱ ግልጽ እንዳልሆነ ስንረዳ አስተማሪውን በማስቆም ማብራሪያ እንጠይቃለን። ያካፈልነውን ትምህርት በሚመለከት ለመናገር ወይም አጽንዖት ለመስጠት ነፃነቱ ነበረን።»

የወንጌል መልእክተኛው ሚስት የማስተማር አገልግሎት

አንዳንድ የወንጌል መልእክተኞች ሚስቶች እነርሱ «እውነተኛ አገልግሎት» ብለው የሚጠሩትን ሥራ ሁልጊዜ ማግኘት ስለማይችሉ ይጨነቃሉ። ጠቃሚ አገልግሎት ለመስጠት ሴቶችን ወይም ልጆችን ማስተማር እንዳለባቸው የሚያስቡ ይመስላል። በአንዳንድ ባህሎችና ሁኔታዎች ይህ አስፈላጊ ሊሆን ቢችልም፥ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ይህ ለወንጌልም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች በጣም ጥሩ መንገድ አይደለም። የቤተሰብ ቡድኖችን በአንድ ላይ ማስተማር ከዚህ እጅግ ይሻላል።

አንዲት የወንጌል መልእክተኛ ሚስት እጅግ ጠቃሚ የሆነ የማስተማር አገልግሎት እንድትሰጥ ምን ማድረግ ትችላለች? በወንጌል ጣቢያ ውስጥ የሚስት የማስተማር ሚና የባሏን ሥራ የሚደግፍ መሆን አለበት። በባሏ አገልግሎት የምትሳተፍበት አንዱ መንገድ እርሱ የሚያስተምርባቸውን ስብሰባዎች ሁሉ መካፈል ነው። በአካባቢው

እናቶችና ልጆቻቸው ወደ ስብሰባ እንዲመጡ የሚጠበቅ ከሆነ፥የወንጌል መልእክተኛ ሚስትና ልጆችም መካፈል አለባቸው። በዚያ ስፍራ በመገኘት ለሕዝቡ በጊዜው የሚሰጠው ትምህርት ምን እንደሆነ ትረዳለች። ሰዎችን በምትጐበኝበት ወይም ሰዎች የእርሷን ቤት በሚጐበኙበት ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ፥ ለሚጠይቁዋቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት ትችላለች። በዚህም ከእግዚአብሔር ቃል ስለተማሩት ነገር ከሰዎች ጋር መወያየት ትችላለች። ይህንን የምታደርገው በቤቷ ውስጥ ዳቦ በምትጋግርበት፥ ምግብ በምታዘጋጅበት፥ የሕክምና ሥራን በምትሠራበት፥ ከሰዎች ጋር በምትገበያይበት ወይም መሠረተ ትምህርት በምታስተምርበት ጊዜ ሁሉ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ሴቶች በቤተሰቦቻቸውና በቤት የዕለት ተዕለት ጉዳዮች ስለሚጠመዱ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ባሎቻቸውን መርዳት አይችሉም። ይህ ከአካባቢው ሕዝቦች የወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሚስቶች ለሚሆኑ ሴቶች በጣም ደካማ ምሳሌ ነው። በእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ከሚያግዱ አንዳንድ የቤት ውስጥ አድካሚ ተግባራት እንዲላቀቁ ሚስቶቻቸውን ስለማያግዟቸው፥ የወንጌል መልእክተኞች ባሎች ተጠያቂነት አለባቸው። ወንዶች ትጉህና ቀናተኛ መሆን ያለባቸው ለራሳቸው የማስተማር አገልግሎት ብቻ ሳይሆን፥ ሚስቶቻቸው በወንጌል ሥራ አማኞችን መንፈሳዊ ምግብ በመመገብ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ጭምር መሆን አለበት።

በአካባቢው ባህል ከተፈቀደ፥ አንዲት ሚስት ባሏ በሚያስተምርበት ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በተጨማሪ ልትረዳው ትችላለች። እነዚህ ጥያቄዎች ቀደም ብላ ከባሏ ጋር የተስማማችበት ወይም ባሏ በሚያስተምርበት ጊዜ አንድ ነገር እንዲብራራ እንደአስፈላጊነቱ የምትጠይቀው ሊሆን ይችላል። የወንጌል መልእክተኛው ሚስት ከአካባቢው ሴቶች መካከል ተቀምጣ ጥያቄ የምትጠይቅ ከሆነ፥ እነርሱም ለመሳተፍ ይበረታታሉ።

የአኔ ባለቤት በዚህ ደረጃ በአገልግሎቴ ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊ ነበረች። በተለይ ከፍተኛ ማብራሪያ በሚጠይቁ ቦታዎች ላይ ታነቃኝ ነበር። እርሷም ችግሮቹን የምታውቀው ስብሰባውን ከሚካፈሉ ሴቶች ጋር በመጫወት ነበር። የመሠረተ ትምህርት በምታስተምርበት ከፍለ ጊዜ በስብሰባዎች ከተሰጡት ትምህርቶች ጋር በቀጥታ በሚያያዙ ርእሰ-ጉዳዮች ላይም ታተኩራለች። ሰዎች በእውነት እውቀት ላይ እንዲመሠረቱ በመርዳት የምታሳልፈውን ጊዜ እጅግ ትወደው ነበር።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ሥዕሎች

በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት የተጠቀምንባቸው የተፈጥሮ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ባህልና፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መልክዓ-ምድር ሥዕሎች በወንጌል ስርጭት የመጀመሪያ ደረጃ ላይም ሊያገለግሉን ይችላሉ። ዋናዎቹ ገጸ ባሕርያት ባህላዊ ዝርዝር ጉዳዮችና በተለይም የታሪኩን ማዕከላዊ ትምህርት የሚያጎሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሥዕሎች ለክፍል አንድ አስፈላጊዎች ናቸው። ሥዕሎቹ ሳሳ ባለ ጨርቅ ላይ የተሣሉ ከሆኑ የሚበረክቱና ለመቀደድም በቀላሉ የማይጋለጡ ይሆናሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚሄዱ ለመሆናቸው እርግጠኛ ሁን። አንዳንድ የልጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል ተብዬዎች በኖኅ መርከብ ወለል ላይ ትላልቅ እንስሳት ተቀምጠው ወይም ከትክክለኛው መርከብ አነስ ተደርጐ በተሠራ መርከብ መስኮት ራሳቸውንና አንገታቸውን ያወጡትን ቀጭኔዎች ያሳያሉ። ለልጆችም ሆነ ለአዋቂዎች የሚቀርቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕሎች ከእውነት ያልራቁ መሆን አለባቸው።

አንዳንድ ጊዜ ሥዕሎች ትምህርቱን ከማገዝ ይልቅ የሕዝቡን አሳብ ሊሰርቁ እንደሚችሉ ልብ በል። ሰዎቹ የሚሰጠውን ትምህርት ከመስማት ይልቅ ስለ ሥዕሎች የሚነጋገሩ ከሆነ፥ ሥዕሉን ከሚታይበት ቦታ ማንሣት ያሻል። ብዙ ጊዜ ግን በማንኛውም ሁኔታ ከሌላ ሥፍራ ተቆርጠው የተወሰዱ፥ ጽሑፍ ያለባቸው ካርዶች ወይም ከጨርቅ የተዘጋጁ ሥዕሎች ጠቃሚ የመረጃ መሣሪያዎች ይሆናሉ፤ ይህም የሚሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ፥ ከእውነታ ያልራቁና በተገቢው ጊዜ የቀረቡ እንደሆነ ነው።

ካርታዎች

በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት የተጠቀምህበትን ያልተወሳሰበ ቀላል የመጽሐፍ ቅዱስ ምድሮችን የሚያሳይ ካርታ ተጠቀም። በክፍል አንድ ያለማቋረጥ ተጠቀምበት። በቅድመ-ወንጌል እንቅስቃሴ ወቅት የተጠቀምህበትን ካርታ ከአጠገብህ አኑርና በሚያስፈልግበት ጊዜ ተጠቀምበት።

የማይንቀሳቀሱ ፊልሞች

አንዳንድ የወንጌል መልእክተኞች ባለቀለም የማይንቀሳቀሱ ፊልሞችን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለማስተማርና ለመከለስ በጣም ጥሩ ሆነው አግኝተዋቸዋል።

በታይላንድ በፓዋ ካረን ነገዶች ውስጥ ይሠራ የነበረው ሮቢን ግርፍዝ የአካባቢ ውበት፥ የእንስሳት፥ የአበባዎች፥ ወዘተ. የመሳሰሉትን የግይንቀሳቀሱ ምስሎችን አዘጋጅቶ ነበር። እነዚህን ምስሎች ዘፍጥረትን በሚያስተምርበት ጊዜ ተጠቀመበት። ዓላማው እነዚህን የለመዱአቸውን ነገሮች በየዕለቱ ሲመለከቱ መንፈሳዊ እውነቶችን ይረዳሉ የሚል ነበር።

ከዚህ በፊት የተሰጡት ትምህርቶችን ለመከለስ እጅግ ግሩም ሆኖ የተገኘው መንገድ በሳምንት አንድ ምሽት ሁለት ወይም ሦስት ታሪኮችን በግይንቀሳቀሱ ፊልሞች ማሳየት ነው።

ከግይንቀሳቀሱ ምስሎች ፊልም ጋር አብረው የሚሄዱ ማብራሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ሮቢን ግርፍዝ እንደሚከተለው ይገልጻል፦

> «ለአንዳንድ የግይንቀሳቀሱ ፊልሞች በቴፕ የተቀረጹ ማብራሪያዎች አዘጋጅቼ ነበር። ይህን በማድረግ ታሪኮቹ ቀደም ብለው ሊታሰቡና በትክክል ሊሠሩ ይችላሉ። ከዚያም የግይንቀሳቀሱ ምስሎች ፊልም መታየት ሲጀምርና ስለሚታየው ነገር ጥያቄ ሲነሣ ቴፕ በማልጠቀምበት ጊዜ እንደሚሆነው አሳቤ በቀላሉ አይብተንም። የተቀረጹ ድምፆች እንደ በግ ድምፅ ዓይነት ያልተለመዱ ርእሰ-ጉዳዮችን ለማስተዋወቅም ይረዳሉ። የተቀረጹ ማብራሪያዎች ሌላም ተግባራዊ ጠቀሜታ አላቸው። አንዱ ወይም ሁለት ጊዜ በራሪ ነፍሳት በግይንቀሳቀስ ፊልም ብርሃን ተስበው ገቡና ጉሮሮዬን በማጥቃት ከፍተኛ ጉዳት አስከተሉብኝ። በአንድ ወቅት ለቀረው ምሽት ድምፄን መጠቀም ስላልቻልሁ ማብራሪያው ሳይሰጥ ቀረ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታና ወቅት በቴፕ የተቀዳ ነገር እጅግ ጠቃሚ ነው።»

ተንቀሳቃሽ ፊልሞች

የተቀንሳቃሽ ፊልሞች ተቀዳሚ ጥቅም ለክለሳ ነው። ስለሆነም፥ ታሪኩን ከመጽሐፍ ቅዱስ ከማስተማር በፊት ፊልም ማሳየት አላዋቂነት ነው። ፊልሙን መጀመሪያ ማየት ለሰዎቹ የሚያስደስት ቢሆንም እንኳ፥ ከታሪኩ የሚገኘው የመሠረታዊ እምነት ትምህርትና የታሪኮቹ መንፈሳዊ ጠቀሜታ ጐልቶ አይታይም።

የምታሳያቸው ፊልሞች ሙሉ ለሙሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል የተዘጋጁና የማይጨምሩ ወይም የማይቀንሱ ለመሆናቸው እርግጠኛ ሁን።

በቴፕ ክሮች ማስቀረጽ

የወንጌል መልእክተኛው ሕዝቡን እያስተማረ ሳለ ትምህርቶቹን ሁሉ መቅረጽ ይችላል። ትምህርቱን መቅረጹ ድክመት የታየበትንና በቃላት፥ በአነጋገር ቅላፄ፥ በማብራሪያ አቀራረብ፥ በትረካ ስልት፥ በማስተማሪያ መረጃዎች አጠቃቀምና በመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትኩረት አካባቢ መሻሻል የሚገባውን ለማየት ይጠቅማል።

ይህ በቴፕ ተቀርጾ የተቀመጠ ነገር ለሚከተሉት ነገሮች ያገለግላል፦

(1) ሁልጊዜ ከሚገኙ ሰዎች መካከል ለአንድ ወይም ለሁለት ክፍለ ጊዜ የቀረ ሰው ቢያጋጥም፥ ያመለጠውን ትምህርት ከተቀረጸው ቴፕ ሊሰማው ይችላል። (2) በሕመም፥ በርቀት ወይም በሌላ ችግር ክፍል መጥተው በሚገባ ሊከታተሉ የማይችሉ ተልኮላቸው ሊሰሙት ይችላሉ። (3) አዳዲስ የመጡ ሰዎችን ያልነበሩበትን ክፍል ከቴፕ በመስማት ሌሎች ከደረሱበት በመድረስ አብረው መከታተል እንዲችሉ ያደርጋል። (4) አዳዲስ አማኞች ወዳልዳኑ ሰዎች በመሄድ ወንጌልን ለመመስከር ሲፈልጉ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በርካታ የወንጌል መልእክተኞች በባትሪ ወይም በእጅ በማዞር የሚሠሩ አነስተኛ የክር ማጫወቻዎች በመግዛት ለሕዝቡ ይሰጣሉ። በሌላ ሁኔታ ግን ሕዝቡ በባትሪ የሚሠራ የክር መቅረጫና መጫወቻ ሊገዙ ይችላሉ።

በቬንዝዌላ የሠራ የወንጌል መልእክተኛ ሜሪል ዳይክ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

> «አንድ ጠዋት ከጕሜ ነገድ ፓንኮ የተባለ ሰው ወደ ቤቴ መጣ። አዛውንት አባቱ ወደ ስብሰባው መምጣት ስላልቻሉ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ሰምተው መረዳት እንዲችሉ ይፈልግ ነበር። ፓንኮ የሰማውን የእግዚአብሔር ቃል ለአባቱ ያካፍል የነበረ ቢሆንም ነገር ግን የእርሱ ትምህርት በቂ እንዳልሆነ አሰበ። አባቱ በቴፕ የተቀረጸውን መልእክት ለመስማት ይፈልጉ እንደሆነ ጠየቅሁት። ፓንኮ ወዲያውኑ በመስማማት ስድስት ተኩል ኪሎ ሜትር ያህል ርቀው ወዳሉት አባቱ እንደሚሄድና ፈቃደኝነታቸውን ጠይቆ መልሱን እንደሚነግረኝ አስታውቀኝ። በዚያን ምሽት ፓንኮ ተመልሶ መጣ። አባቱ የተቀረጸውን ድምፅ ለመስማት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገለጠ።
>
> «የቴፕ መቅረጫዎችን ጥቅም በሚገባ ከመረዳቴ የተነሣ፥ አሥር በእጅ በማዞር የሚሠሩ ሞዴሎች እንዲመጡልኝ ለወንጌል ቀረጻ አገልግሎት ልኬ ነበር። እስከዚህ ድረስ የተቀረጸ መልእክት በማስቀመጡ ጉዳይ ላይ አስበንና ተጨንቀን አናውቅም ነበር።

አሁን ግን ፑሚዎች የቴፕ ክሮችን ለማዳመጥ የሚፈልጉ ይመስላል። ወዲያውኑ ምን ዓይነት ታላቅ መሣሪያ እንደሆኑ አየን። ምክንያቱን ላብራራው። ፑሚዎች የሚኖሩት ከ4–10 የሚደርሱ ቤተሰቦችን በያዙ ቡድኖች ነው። እያንዳንዱ ቡድን ከ5–8 ኪሎ ሜትር ያህል ከሌሎች ቡድኖች ርቆ ይኖራል። በትምህርት ፕሮግራማችን በተለየ ሁኔታ አትኩረን የነበረው በአንድ ቡድን ላይ ነበር። የቴፕ መቅረጫዎችን በመጠቀም የእግዚአብሔር ቃል በየመንደሩ መዳረስ ችሎ ነበር።

«ስለዚህ ጉዳይ የመጀመሪያው የፑሚ አማኝ ከነበረው ራሞን ጋር ስነጋገር አሣቡን በአንዴ ተቀበለው። በቴፕ የተቀረጹትን ትምህርቶች ለማስተማር እችል ዘንድ ሊረዳኝ እጅግ ፈቃደኛ ነበር። ስለዚህ ጀመርን። ትሬቨር ማክኢልዌይን በዘፍጥረት ላይ ከጻፋቸው ዝርዝር ትምህርቶች ጀምረን በተከታታይ ቀጠልን። እኔ አንድ ነጥብ አስተምርና ያንኑ ነጥብ ራሞን በስፋት ያብራራዋል። በመቀጠል ሌላ ነጥብ አስተምራለሁ። ራሞን ትኩረት ሰጥቶ ይገልጸዋል። በዘወትር የማስተማር ተግባሬ እንደማደርገው በርካታ ተግባራዊ ምሳሌዎችን በመጠቀም የቴፕ ትምህርት ጊዜያትን ሕይወት ያላቸው ለማድረግ የቻልነውን ሁሉ ጥረት አደረግን።

«ብዙ ሳንቆይ ከወንዙ ከፍ ብሎ ባለው መንደር የሚገኝ የፑሚ ሰው ቃሉን ለመስማት የሚችልበትን የክር ማጫወቻ ጠየቀን። ከአንድ ሳምንት በኋላ ደግሞ ከመንደር አለቆች አንዱ በቴፕ የተቀረጹትን ትምህርቶች ለመስማት ፈልጎ ወደ እኛ መጣ። በአሁኑ ጊዜ ቃሉ በተቀረጹ ክሮች አማካይነት ወደ ሦስት መንደሮች ይላካል።

«ትምህርት ለመስጠትና የሚሉትን ለመስማት በሳምንት አንድ ቀን ወደ እነዚህ ሦስት መንደሮች እሄዳለሁ። በቂ ጊዜ ወስጄ ጥያቄዎችን በማቅረብ የግንዛቤ ደረጃቸውን አረጋግጣለሁ። ለጥያቄዎቼ የሚሰጡኝ መልሶች እየተማሩ መሆናቸውን በግልጽ ያመለክቱኛል።

«ቴፕ ሪከርደሮች ቃሉ ለፑሚ ሕዝቦች እንዲደርስ እውነተኛ አጋዥ ሆነዋል። አሁንም ናቸው። እነዚህን መሣሪያዎች ወንጌልን ለማስፋፋት ልንጠቀምባቸው ስለቻልን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።»

ጆሰንና ሸርሊ በርኪን በፊሊፒንስ ሚንዳናአ የሚገኘው እጅግ ኋላ ቀር የሆነ ታላ አንዲግ የሚባል ዘላን ጎብረተሰብን በወንጌል መልእክተኛነት ያገለግሉ ነበር። ባለማቋረጥ የሚንቀሳቀሰውን ይህን ጎብረተሰብ ለማገልገል የቴፕ መቅረጫዎችና በእጅ በማዞር የሚሠሩ የክር ማጫዎቻዎች እጅግ ውጤታማ መሣሪያዎች ሆነው አገልግለዋል።

ጆሰን ወደ ቤቱ ሲመጡና ምሽቱን አብረውት ሲቆዩ ሕዝቡን ያስተምራቸው ነበር። አብዛኛውን የወንጌል ስብከት የሚያካሄደው ሰዎችን በአካል በማግኘት አልነበረም። ትምህርቱን በቴፕ ክሮች ይቀርጽና ሰዎቹ ይዘውት እንዲሄዱ ይሰጣቸዋል። ጌታ እግዚአብሔር ብዙ ሰዎች ቃሉን በዚህ መንገድ እንዲሰሙ በማድረጉ በርካታ የታላ አንዲግ ሕዝቦች ዛሬ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።

በሰባቱ ደረጃዎች የሚሰጡትን ትምህርቶች በቴፕ ክሮች በመቅረጽ አንድ የቴፕ ክሮች ክምችት ከፈትህ ማለት ነው። እነዚህ የቴፕ ክሮች የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ለአዲስ አማኞችና ለበሰሉ ክርስቲያኖች በሚያስተምርበት ጊዜ ትልቅ ዕርዳታ ይሆኑታል።

በርካታ የወንጌል መልእክተኞች ትምህርቶቻቸውን ሁሉ ቤቴፕ ክሮች መቅረጽ ጠቀሜታ እንዳለው ዘግበዋል። እነዚህን የተቀረጹ ክሮች በመጠቀም ሰዎች በተለያዩ ደረጃዎች የተዘጋጁትን ትምህርቶችን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ በተደጋጋሚ ለበርካታ ጊዜያት ለመስማት ዕድል አግኝተዋል።

ዕቃዎችን በመጠቀም ማስተማር

የተለያዩ ዕቃዎችን ለትምህርት መርጃ መሣሪያነት መጠቀም የሰዎችን ቀልብ ለመሳብና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለማብራራት በጣም ጥሩ ነው።

በፓፑዋ ኒው ጊኒ ተራራዎች በፎሬ ነገድ መካከል የሚሠሩትን ጆንና ኬይ ቶልማንን በጐበኘሁበት ጊዜ ለትምህርት መርጃ መሣሪያነት መጠቀም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በግልጽ ተመልክቼአለሁ። የፎሬ ሕዝብ የሰው ልጅ በአዳም ያለመታዘዝ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ማለፍያ ግንኙነት ተቋርጦበት እንደሞተ የሚያስረዳውን እውነት ለመጨበጥ አልቻሉም ነበር። ጆን አነስተኛ የዛፍ ቅርንጫፍ እንዲሰብርና በማስረጃነት እንዲጠቀም አሳብ አቀረብሁ።

የማስተማርያ ክፍለ ጊዜው ሲጀመር ከፊት ለፊቴ የተቀመጡ ሁለት አዛውንቶች በዝግታ በማውጋት የእግር ጥፍሮቻቸውን በማጽዳትና ሰውነታቸው ላይ በማከኩ ተግባር ላይ ስለተሰማሩ፥ ለሚሰጠው ትምህርት የነበራቸው ትኩረት እጅግ አነስተኛ ነበር። በግራዬ በኩል ደግሞ ስድስት ሴቶች ከልጆቻቸውና ከሕፃናቶቻቸው ጋር ተቀምጠው ነበር። አትኩሮታቸው የነበረው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሳይሆን በሕፃናቶቻቸው ላይ ነበር።

የእነዚህን አዛውንቶችና እናቶች ደካማ የመከታተል ፍላጐት እየታዘብሁ ሳለሁ፥ ወዲያውኑ ቀልባቸውን ሰብስበው ይሰሙ ጀመር። አዛውንቶቹ የሚያስተምረው ሰው በእጆቹ የያዘውን ነገር ለመመልከት

አንገቶቻቸውን እያሰገጉ ጆን የሚናገረውን በአትኩሮት ያዳምጡ ጀመር። ሴቶቹም ሕፃናት ልጆቻቸውን ረስተው ለማየትና ለመስማት ወደፊት ተጠጉ። ይህን ልዩነት ያመጣው ምን ነበር? ጆን የአንድ ዛፍ ቅርንጫፍ ሰብሮ ወደምንሰበሰብበት ቦታ አምጥቶ ነበርና ይህ ለውጥ የተከሰተው ያንን ባነሣበት ወቅት ነበር። ጆን ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ የዛፉን ቅርንጫፍ በወለል ላይ መልሶ አስቀመጠው። ወዲያውኑ አዛውንቶቹና ሴቶቹ በአቅራቢያቸው ባገኙት ነገር ለመጠመድ ወደኋላ ዘንፈል እያሉ ተቀመጡ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ጆን የዛፉን ቅርንጫፍ እንደገና ሲያነሣ በዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ የነበረው ጉጉት ወዲያው ተደገመ።

ድራማ (ተውኔት)

ታሪኩን እየተናገርህ ሳለህ ወይም በየታሪኮቹ መካከል ላይ በድራማ ታሪኩን ግለጽ። ድራማ በንግግር ከሚቀርብ ትምህርት ይልቅ የአድማጮችን አትኩሮት የመያዝና አሳባቸውን የመሰብሰብ ብቃት አለው። ይህም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ክልልና ለአድማጮቹ ባህል ተቀባይነት ባለው መንገድ ብቻ የሚቀርብ መሆን አለበት። ድራማ በአንዳንድ ባህል ተቀባይነት ያለው የመግባቢያ መንገድ አይደለም። ነገር ግን በአካባቢው አገልግሎት ላይ የሚውል ባይሆንም እንኳ በሰዎች ዘንድ መረዳትንና አድናቆትን እንዲያገኝ ማድረግ ይቻላል። የአካባቢውን ሰዎች በመጀመሪያ ቀላል ድራማ በማሳየት ተቀባይነቱና ጠቃሚ መሆኑን ሲረጋገጥ እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ይቻላል።

በፓፑዋ ኒው ጊኒ በሴፒክ ክልል የሚኖሩትን የቢሶሪዮ ጓላቀር ነገድ አባላት ያገለገሉት ቦብ ኪነልና ጆርጅ ዎከር የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በመግለጥ ለማስተማር ቀላል ተውኔታዊ ጭውውቶች ያቀርቡላቸው ነበር። ጆርጅ ስለተውኔታዊ ጭውውቶች የሚከተለውን ዘግቧል፦

> «በማስተማር ሂደት ላይ ድራማ የግድ የሚባል ሳይሆን፥ እንደ አንድ አማራጭ የሚታይ ነው። ለአንዳንድ ነገዶች ድራማ አማራጭ ማስተማሪያ ላይሆንም ይችላል። ለብዙዎች ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እውነትን ለመረዳት ተውኔታዊ ጭውውቶች እገዛ ያደርጋሉ። ይህም ሆኖ በአካባቢው ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማይቻል የሚመስለውን ነገር የሚያከናውነው ተውኔታዊ ጭውውታችን ወይም እኛ እንዳይደለን ልብ ልንል ይገባል። ጌታ ነው። የቃሉን እውነት ለሰዎች ልብና ሕይወት ተግባራዊ ለማድረግ በእርሱ ተደገፍ። በተውኔታዊ ጭውውቶችህ ላይ አትደገፍ።
>
> «ተውኔታዊ ጭውውቶችን ስታዘጋጅ፥ በጌታ ምሪት የተለያዩ ፈጠራዎችን ተጠቀም። ሁልጊዜ በሚገባ ተዘጋጅ። የሚያስፈልጉ

ነገሮች ሊዘጋጁና የተውኔቱ ክፍሎች ሁሉ በሚገባ ሊታወቁ ይገባል።

«በተውኔታዊ ጭውውቱ ውስጥ ዋናዎቹ ተዋንያን አንተና አብረውህ የሚሠሩ ሰዎች መሆናቸው የሚያጠራጥር አይደለም። የአካባቢውን ቋንቋ በሚገባ አጣርተው የማያውቁ አብረውህ የሚሠሩ ሰዎች እንኳ በዚህ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። የሚያስፈልጉህ ሰዎች በርክተው በወንጌል መልእክተኛው ቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች ቁጥር ካነሰ፥ የቀረውን ለማሟላት ከሕዝቡ መካከል እንኳ መጠቀም ትችላለህ። አሠራሩ ከገባቸው ዕድሜያቸው ከ14–17 የሆኑ ወጣቶች ፈቃደኛነቱም ብቃቱም አላቸው።

«ስኪታማ ተውኔት ለመሥራት ቁሳቁሶች መብዛት የለባቸውም። መሠረታዊና ቀላል መሆናቸው የበለጠ ጥሩ ነው።

«ቁሳቁሶቹ ስፍራቸውን ከያዙ በኋላ፥ ትዕይንቱን ከመጀመራችሁ በፊት የታሪኩን መነሻ በሕዝቡ አእምሮ አስቀምጡ። ተዋንያኑንና የሚሠሩትን ክፍል አስተዋውቁ። ተውኔቱ ከመጀመሩ በፊት የተውኔቱ መቼት (መቼ እና የት) ግልጽ መሆኑን አረጋግጡ።

«ተውኔቱን ስታቀርቡ፥ ሕይወትን እንደሚሰጠው በእግዚአብሔር ታመኑ። የምትናገሩአቸው ቃላት ግልጽ ትርጉም ይኑራቸው። የአካባቢው ሕዝብ የሚጠቀምበትን አካላዊ ቋንቋና ሥርዓት ተጠቀሙ። የእነርሱን ምሳሌያዊ አነጋገር ተጠቀሙ። በራሳቸው የአነጋገር ዘይቤ መልእክቱን አስተላልፉ።

«በተውኔቱ መጨረሻ ወይም በየትዕይንቱ መካከል ትምህርትና ማብራሪያዎችን ስጡ። ለቀረበው ድራማ በቂ ትርጉም መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የባላገር ሰዎች ድራማውን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊረዱ ወይም የተሳሳተ ትርጉም ሊሰጡት ስለሚችሉ ነው። እንደ እነዚህ ዓይነት ሕዝቦች ተጨባጭነት በሌለው ነገር የሚያምኑና የሚመለከቱት ነገር ጥልቅ ስሜት የሚያሳድርባቸው ናቸው። ስለዚህ የሚያገለግላቸው የወንጌል መልእክተኛ ያለማቋረጥ በንቃት ሊጠብቃቸው የሚችል፥ እንዴት እንደሚጠቀምበት በጥበብ የሚሠራና ሁልጊዜ የሕዝቡን እውነተኛ ፍላጐትና አስተሳሰብ የሚረዳ መሆን አለበት።

«ተውኔታዊ ጭውውቶችን እንደ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ባትጠቀም እንኳ፥ በድምጽህና በአካላዊ እንቅስቃሴህ የሕዝቡን ቀልብ ልትስብና ታሪኩን ሥዕላዊ በሆነ አገላለጽ ልታቀርብ ትችላለህ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ክልል ውጪ ላለመውጣት መጠንቀቁ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርያትን ስሜታዊ ድርጊቶችና ምላሾች በዓይነ

ሕሊናህ ለማየት ምናባዊ አስተሳሰብህን ተጠቀም። በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ፈርተው፥ ተደንቀው፥ ተገርመው፥ ተቆጥተው፥ ተደስተው ወዘተ... እንደሆነ፥ ይህንኑ በባህላዊ መንገድ በሚገባ ግለጽ። ዝም ብለህ ከመቀመጥ ይልቅ፥ ተነሥተህ በመንጐራደድ በምትናገረው ታሪክ ውስጥ የተመለከቱት ገጸ ባሕርያት የፈጸሙትን ድርጊት አሳይ። ይህ ለተፈጸመው ታሪክ ሕይወትና ስሜት ይጨምርለታል። ለምሳሌ አዳምና ሔዋን «አዳም ወዴት ነህ?» የሚለውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው እንዴት እንደተሸሸጉ የሚናገረውን ታሪክ በምትተርክበት ጊዜ፥ አዳምና ሔዋን እንዴት እንዳፈሩና ራሳቸውን ለመሸሸግ እንደሞከሩ ለማሳየት አፍሮ እንደሚደበቅ ሰው ፊትህን በእጆችህ ሸፍነህ ከቤቱ በስተ ኋላ ለመደበቅ ሞክር። የይስሐቅን ለመሥዋዕት የመቅረብ ታሪክ ስትተርክ፥ አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ምን ያህል ተዘጋጅቶ እንደነበር ለማሳየት ቢላዋ ይዘህ እጅህን አንሣ።»

በጊዜ ቅደም ተከተል የቀረቡ ስሞች ሠንጠረዥ

ፓላዋኖዎችን በምናስተምርበት ጊዜ በክፍል አንድና ሁለት የምናስተምራቸውን ክስተቶችና ስሞች የያዘ ሠንጠረዥ አዘጋጅተን ነበር። ለሠንጠረዡ የተጠቀምንበት ነጭ ጨርቅና በውኃ የማይለቅ ቀለም ያለው ብዕር ነበር።

ሠንጠረዡን በአንድ ረጅም ጨርቅ ላይ ሥራና ስብሰባው በሚካሄድበት ክፍል ግድግዳ ላይ ለጥፈው። ክፍሉ ጠባብ ከሆነ ሠንጠረዡን ለሁለት በመክፈል በትክክለኛው ቅደም ተከተል ላይና ታች አድርገህ ስቀለው። እኛ ላዘጋጀነው ሠንጠረዥ ግድግዳው ላይ በቀላሉ እንደታሰረ የእኔ ባለቤት በስተመጨረሻና በየመሃሉ ሸምቀቆ ሠርታለት ነበር።

ሰው ሁሉ በግልጽ ሊያየው እንዲችል የሠንጠረዡን ጽሑፍ ትላልቅ አድርገው።

ትምህርቱ በጊዜ ቅደም ተከተል በተሰጠ ቁጥር ሠንጠረዡን እየዘረጋኸው ቀጥል። ሕዝቡ እንዲያየው የምትዘረጋው ከዚህ ቀደም የተማሩትንና አሁን በመማር ላይ ያሉትን ብቻ ይሆናል።

ሰው ሁሉ በግልጽ ሊያየው እንዲችል የሠንጠረዡን ጽሑፍ ትላልቅ አድርገው።

ትምህርቱ በጊዜ ቅደም ተከተል በተሰጠ ቁጥር ሠንጠረዡን እየዘረጋኸው ቀጥል። ሕዝቡ እንዲያየው የምትዘረጋው ከዚህ ቀደም የተማሩትንና አሁን በመማር ላይ ያሉትን ብቻ ይሆናል።

እግዚአ ብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ	የእግዚአ ብሔር መላእክ ት ሉሲፈር	ሰይጣንና አጋንንቱ	አዳምና ሔዋን	ቃይን አቤል ሴት ሄኖክ	ኖኅ ሴም ካም ያፌት	ባቢሎን	አብራሃ ም ሳራ ሎጥ	መልከ ጼዴቅ አጋር እስማኤል
ይስሐቅ ዔሳው ያዕቆብ ዮሴፍ	ሙሴ አሮን ኢያሱ	መሳፍንት	ሳዖል ዳዊት ሰሎሞን	ነገሥታ ት ዮናስ ነቢያት	መጥም ቁ ዮሐንስ ማርያም ዮሴፍ	ኢየሱስ 12ቱ ሐዋርያ ት	ጳውሎስ	ቤተ ክርስቲያን

የመልከ ጼዴቅ፥ የአጋርና የእስማኤል ታሪኮች የሚጨመሩ እንጂ በክፍል አንድ የሚነገሩ አይሆኑም። ይህ ቅደም ተከተላዊ ሠንጠረዥ ክፍል ሁለትንም ለማስተማር ስለሚያገለግል እነዚህን ስሞች በሠንጠረዡ ላይ ሊጻፉና ታሪኮቹ ቆየት ብለው እንደሚቀርቡ ለሕዝቡ መግለጫ ሊሰጥ ወይም በሠንጠረዡ ክፍት ቦታ ተትቶ የክፍል ሁለት ትምህርት ሊሰጥ ሲል እንዲጻፍ ሊደረግ ይችላል።

የነቢያት መልእክት ሠንጠረዥ

የክርስቶስን ሕይወት ከአዲስ ኪዳን በምናስተምርበት ጊዜ ስለ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶችን በሠንጠረዥ መልክ ማቅረብ የሚረዳ ይሆናል።

በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶችን ከብሉይ ኪዳን ማጠቀሻዎቻቸው (ከሥር ተሰጥተዋል) ጋር ጻፍ፤ የአዲስ ኪዳን ማጣቀሻዎችን ግን አስቀር። የአዲስ ኪዳን ማጣቀሻዎችን መጻፍ ጥሩ የሚሆነው የአዲስ ኪዳን ታሪክን በማስተማር የትንቢቶቹን መፈጸም በምትናገርበት ጊዜ ነው። በዚህ ዓይነት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን (ስለ ኢየሱስ የተነገሩት) በምትደርስባቸው ወቅት ከጻፍሃቸው፥ አድማጮችህ ቀስ በቀስ እንዴት በክርስቶስ ሕይወት እንደተፈጸሙ ይመለከታሉ።

የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ተዘርዝረው የተቀመጡት በክርስቶስ ሕይወት በሚፈጸሙበት ቅደም ተከተል ነው።

ሠንጠረዥ ጉባኤው በሙሉ ሊያየው አስከሚችል ትልቅ ይሁን። በቤት ስብሰባዎች አገልግሎት ላይ ይውሉ ዘንድ ትናንሽ ሠንጠረዦችንም ማዘጋጀት ይቻላል።

የምትሰበሰቡበት ቦታ በቋሚነት የምትጠቀሙበት ከሆነ ሕዝቡ ሁልጊዜ ይመለከተው ዘንድ ሠንጠረዡ በመሰብሰቢያው ቤት ግድግዳ ላይ ይደረግ። ይህም ሲሆን፥ ከክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ስለተግርሃቸው ዋና ዋና ድርጊቶች የሚያስታውስ ቋሚ ማሳሰቢያ ይሆናል። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ የሚፈጽም ታማኝ አምላክ መሆኑን ይመሰክራል።

እግዚአብሔር ስለ ነፃ አውጪው የተናገረው		የእግዚአብሔር ቃል ሲፈጸም
ኢሳ. 9፡7	ከዳዊት ዘር ይሆናል።	ማቴዎስ 1፡1
ኢሳ. 7፡14	ከድንግል ይወለዳል	ማቴ. 1፡18–25
ሚክ. 5፡2	በቤተ ልሔም ይወለዳል	ማቴ. 2፡1
ሆሴ 11፡1	ወደ ግብፅ ይሸሻል	ማቴ. 2፡14
ኢሳ. 11፡2	ከባሕርያቱ ጥቂቶቹ	ሉቃስ 2፡52
ኢሳ. 53፡4፥5	ለሌሎች መከራን ይቀበላል	ዮሐ. 10፡11
መዝ. 41፡9	ወዳጁ አሳልፎ ይሰጠዋል	ማር. 14፡10፥11
ዘካ. 11፡12፥13	በሠላሳ ብር ይሸጣል	ማቴ. 26፡14፥15
መዝ. 27፡12	ሐሰተኛ ምስክሮች ይከሱታል	ማር. 14፡56፥57
ኢሳ. 50፡6	ይተፉበታል በጥፊ ይመቱታል	ማር. 14፡65
ኢሳ. 53፡7	በከሳሾቹ ፊት ዝም ይላል	ማር. 15፡3–5
ኢሳ. 53፡3	አይሁዶች አይቀበሉትም	ማር. 15፡9–14
መዝ. 69፡4	ያለምክንያት ይጠላል	ማር. 15፡10
መዝ. 22፡16	እጆቹና እግሮቹ ይቸነከራሉ	ማር. 15፡24
መዝ. 22፡18	በልብሶቹ ዕጣ ይጣጣላሉ	ማር. 15፡24
ኢሳ. 53፡12	ከክፉዎች ጋር ይሞታል	ማር. 15፡27
መዝ. 22፡6–8	ያፌዙበታል ያላግጡበታል	ማር. 15፡29–32

ኢሳ. 53፡9	መቃብሩ ከሀብታሞች ጋር ይሆናል	ማር. 15፡43–46
መዝ. 16፡10	ከሞት ይነሣል	ማር. 16፡6
መዝ. 68፡18	ወደ ሰማይ ያርጋል	የሐዋ 1፡9

ባህላዊ መግለጫዎችን መጠቀም

ፍጹሙ መምህር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ እውነቶችን ለመግለጥ የተጠቀመው ለዕለታዊ ግልጋሎት በየዕለቱ የሚውሉትን ዕቃዎች፥ ተራ ሁኔታዎችና የሰዎች ግንኙነቶች ነበር። ታሪኮቹ፥ መግለጫዎቹና ምሳሌዎቹ የተወሰዱት ከአድማጮቹ ተለምዶአዊና ባህላዊ ልምምዶች ነበር። ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ የተለያዩ ዓይነት ዓሦችን ስላጠመዱና ቁጭ ብለው ስለሚለዩአቸው ዓሣ አጥማጆች ተናግሯል። ዘራቸውን ስለሚዘሩ፥ ስለሚያጭዱና ስለሚከምሩ ገበሬዎች፥ በጕቻቸውን ስለሚንከባከቡና ስለሚጠብቁ እረኞችም ተናግሯል። ስለጠፋው ልጅና በቤቱ ታማኝ ስለነበረው ልጅ ደግሞም ስለ ተፈጥሮአዊው የአባት ፍቅር ገልጾአል። ድሪም ጠፍቶባት ስለምትፈልግ ሴት፥ በገበያ ቦታ ጋብቻንና ቀብርን የሚፈጽሙ ስለሚመስሉት ልጆች፥ በወንበዴዎች ስለተደበደበና በሳምራዊ ሰው ቸርነት ስለተደረገለት መንገደኛ ተናግሯል። ለልጁ የሠርግ ግብዣ ስላዘጋጀ፥ በአገልጋዮቹ ላይ ስለፈረደና ቅጣትን ስላደረገ ንጉሥ ታሪክ ተናግሯል።

ጌታ ኢየሱስ ስለ አበቦች፥ ሣሮች፥ ወይን ግንድ፥ እህሎች፥ አዕዋፋት፥ ዓሦችና እንስሳት ተናግሯል። ስለ ዝናብ፥ ጕርፍ፥ ነፋሳትና መልካም የአየር ሁኔታ ተናግሯል። ስለወይን ጠጅ፥ ውኃ፥ ዳቦ፥ አዲስና አሮጌ ልብስ፥ ቤቶችና መቅረዞች ተናግሯል። እነዚህን ሁሉና ሌሎችንም በርካታ ተፈጥሮአዊና ዕለት በዕለት የሚታዩትን ዕቃዎች የተጠቀመው በአድማጮቹ ግንዛቤ ላይ አብርሆት ለማከልና በተፈጥሮአዊ ዓይን የማይታዩትን መንፈሳዊ ነገሮች እንዲመረምሩ ለማገዝ ነበር።

እኛም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን መንፈሳዊ እውነቶችና ትርጉሞችን ለማስረዳትና አጉልቶ ለማሳየት በአካባቢው የሚገኙትን ዕቃዎች፥ ባህላዊ ታሪኮችና የተለመዱ ዕለታዊ ሁኔታዎችን መጠቀም አለብን።

በወንጌል መልእክተኞች የሚነገሩ አንዳንድ ታሪኮች ልብ–ወለዳዊና የገጸ ባሕርያቱ ገጠመኞችም ከአድማጮቻቸው የዕለት ተዕለት ከንውን ያለፉ ቢሆኑም፥ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ባህላዊና ሚዛነ–ሕሊናዊ ተግባራዊነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ለፓላዋኖዎች

ዋናው ገጸ ባሕርይ ፕሬዘዳንቱን ለማየት ወደ ናይሮቢ የሄዱበትን ታሪክ ነገርኋቸው። ይህ ለብዙ ፖላዋኖዎች የማይታሰብ ጉዳይ ቢሆንም እንኳ፥ ጥቂት ፖላዋኖዎች ናይሮቢ ሄደው ስለሚያውቁ የሚቻል ነገር ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ለመግለጽ ልብ ወለዳዊ ታሪኮች ሊያገለግሉ ቢችሉም፥ ከሁሉ የተሻለው መግለጫ በእውነተኛ ሕይወት ውስጥ የሚታይ ነው።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትርጉም

ብዙ የወንጌል መልእክተኞች የአዲስ ኪዳንን መተርጉምን የሚደገፉ ቢሆኑም፥ አንዳንዶች የብሉይ ኪዳን ትምህርት ለመሸፈን ብቸኛው ምንጭ አድርገው የሚጠቀሙበት በወንጌል መልእክተኛው በራሱ ስልት የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነው። በበኩሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ጠቃሚነት የምረዳው ቢሆንም፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንጻር በሚቻልበት ስፍራ ሁሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መተርጉም አለባቸው።

ምንም እንኳ የወንጌል መልእክተኞቹ በአካባቢው ላለች ቤተ ክርስቲያን ሙሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ለመተርጉም ጊዜ ባይኖራቸውም፥ የተቻላቸውን ያህል የብሉይ ኪዳን ትርጉሞችን አዘጋጅተው ለአማኞች ለመስጠት መሞከር አለባቸው። ጳውሎስ በግልጽ እንዳስቀመጠው፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተዛማጅነት ያላቸውና እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን የሰጠን መልእክቶች ናቸው። በዚህ በመጨረሻው ዘመን ለምንኖር ሰዎችም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያስፈልጉናል፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ እንደተጻፉበት ዘመን ሁሉ አሁንም የእግዚአብሔር ድምፅ ናቸው (ሮሜ. 15፡4፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡6፥11)።

«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ... ይጠቅማል» (2ኛ ጢሞ. 3፡16)። ስለዚህ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ገንቢ፥ «ቃሉን ስበክ...» ሲል ኃላፊነት ሰጥቶታል (2ኛ ጢሞ. 4፡2)። ለእኛም የተሰጠን ይኸው ኃላፊነት ነው። የወንጌል መልእክተኞች ሌሎችን ለማስተማር ለሚችሉ ለታመኑ የአካባቢው ሰዎች ቃሉን በኃላፊነት መስጠት አለባቸው። ይሁንና፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በራሳቸው ቋንቋ ካልተተረጐሙ፥ ይህ ኃላፊነት ለአካባቢው መሪዎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በተመለከተ ሊሰጥ አይችልም። «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» ለማለት ሥልጣን አይኖራቸውም። የእኛን የብሉይ ኪዳን ታሪኮች አቀራረብ ከፍ በማድረግ ከተተረጐሙት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እኩል ማድረግ ተገቢ አይደለም። «የእግዚአብሔር ቃል» የሚለውን ሐረግ የምንጠቀመው

በመንፈስ ቅዱስ አንቀሳቃሽነት በመጀመሪያ በተሰጡት የተተረጐሙትን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመግለጽ ብቻ ነው።

በተጨማሪም፥ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ በሥራ ላይ ያለችውን የአካባቢ ቤተ ክርስቲያን ማስተማሩን ይቀጥላል። የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን ብቻ ተመልክተው ቢሆን ኖሮ ሊገነዘቡት በማይችሉበት መንገድ ከዚህ ቀደም ያልተመለከቱትን የእውነት ሀብት የበለጠ ጠልቀው እንዲመለከቱ ይመራቸዋል። የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ክፍሎችን ተርጉመን ካላዘጋጀን የአማኞች ዕድገት፥ እምነትና አካሄድ በጣም ውስን ይሆናል።

የክርስትና መሠረታዊ እምነት ትምህርትን እግዚአብሔር ከገለጠበት ታሪካዊ መቼት ለይቶ ማቅረብ መልካም እንዳልሆነ ሁሉ፥ ብዙውን ጊዜ በረቀቀ ጥበብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተመረጡ የመንፈስ ቅዱስ ቃላት አማካኝነት የተሳሰረውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ባላዘሉ ታሪኮች ላይ ብቻ መደገፍ አለማስተዋል ነው።

የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን ብቻ ለአካባቢው ሕዝብ ማቅረብ እግዚአብሔር ለእኛ እንደተናገረው ሁሉ ለእነርሱና ለቀጣዩ ትውልድ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚናገርበትን ዕድል ማገድ ነው። ታሪኮች ያሉበት የእኛ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ሥልጣን ሊኖረው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ለገቡት ሁሉ፥ «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም። በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» (1ኛ. ጴጥ. 1፡23) ይላል። የእግዚአብሔር ኃይልና ሕይወት በቃሉ ውስጥ ተሰውረዋል። በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ የተጻፈው ቃሉን በባለቤትነት የያዘው መንፈስ ቅዱስ ነው (የሐዋ. 20፡32)።

ለእያንዳንዱ የማስተማር ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የወንጌል ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በአካባቢው ቋንቋ ማግኘት ካለመቻሉም በላይ የግድ አስፈላጊም አይደለም። ለወንጌል ሥራ ክፍል አንድ ለትምህርቱ የተለዩ የአዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ትርጉም ማዘጋጀት ብቻ ያስፈልጋል። (እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በእያንዳንዱ የክፍል አንድ ትምህርት መጀመሪያ ላይ ተዘርዝረዋል። በዚህ መጽሐፍ በጥራዝ 3 ኋላ ይቀርባሉ።) እነዚህ ክፍሎች በዚህ መጽሐፍ ጭማሪዎች ለብቻቸው በዝርዝር ሰፍረዋል። ተርጓሚው የሚያካትተው እነዚህን ክፍሎች ብቻ ከሆነ፥ ለንባብ የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎቹን በትምህርት ክፍለ ጊዜዎቹ ለመስጠት መቻል አለበት። ለሚቀጥሉት ደረጃዎቻችን ተጨማሪዎቹን ክፍሎች እንደየአስፈላጊነቱ መጨመር ይቻላል።